# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 123 ጥር 3 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - በእዮብ ተፈራ

# ኢትዮጵያና ቻይና

## የሁለትዮሽ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር እንደሚሠሩ አስታወቁ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ቻይና ለረጅም ዓመታት የቆየውን ወዳጅነታቸውንና የትብብር መንፈሳቸውን በማጎልበት ስትራቴጂካዊ ግንኙነታቸው ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን አስታወቁ፡፡ የሁለቱ ሀገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ትላንት በአዲስ አበባ መክረዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ትናንት ከቻይና አቻቸው ቺን ጋንግ ጋር መክረዋል፡፡ ሁለቱ አገራት ለረጅም ዓመታት ያካበቱትን ስትራቴጂካዊ የትብብር አጋርነታቸውን ይበልጥ አጠናክረው ወደ ተግባር ቀይረው እንደሚሠሩ ሚኒስትሮቹ በሰጡት የጋራ መግለጫ አስታውቀዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፤ ከሚኒስትሩ ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ በዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ቀጣናዊና ሀገራዊ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በዝርዝር ፍሬያማ ውይይት ማድረጋቸውን በመግለጫቸው አንስተዋል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላትን በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

ቻይናና ኢትዮጵያ ለረጅም ዓመታት የዘለቀ ጠንካራ ግንኙነት አላቸው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ባለፉት ዓመታት ይህንኑ የሚመጥን በጠንካራ ግንኙነትና ትብብር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንደነበራቸውም ጠቅሰዋል፡፡ የሁለትዮሽ ግንኙነቱ የበለጠ የሚጎለብትበትን መንገድ በዝርዝር ተመልክተናል ያሉት ያሉት አቶ ደመቀ፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል ስትራቴጂካዊ የትብብር አጋርነት መፈረሙንም አስታውቀዋል፡፡

ኢትዮጵያና ቻይና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ዮሃንስ ወጋሶ ወዳጆ

## በጦርነት ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች ትምህርትን መልሶ የማስጀመር ሥራ እየተከናወነ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በጦርነቱ ምክንያት ትምህርት ተቋርጦባቸው የቆዩ የሰሜኑ የሃገራችን አካባቢዎችን ትምህርት የማስጀመርና የፈረሱ አደረጃጀቶችን መልሶ የማጠናከር ሥራ እየተፋጠነ እንደሚገኝ በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ፕሮግራሞችና መሻሻል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዮሃንስ ወጋሶ ወዳጆ ገለጹ፡፡

በጦርነት ውስጥ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## "የተጀመረውን ሰላም ለማፅናት ሁሉም ወገኖች ሊረባረቡ ይገባል"

### - ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ



**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የሰላምን ውድ ዋጋ በመረዳት የተጀመረውን የሰላም ዕድል ከዳር ለማድረስ እያንዳንዱ ዜጋ ሊረባረብ ይገባል ስትል ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ገለፀች፡፡ የትግራይ ተወላጅ አትሌቶች፣ የፌደሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና የሥራ ክፍል ኃላፊዎችን ያካተተና በረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ የተመራ ቡድን ትላንት ወደ መቀሌ አቅንቷል፡፡

"የተጀመረውን ሰላም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## መረጃን በ10 ቀናት ለመስጠት የሚያስገድድ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጀ

**አስመረት ብሥራት**

አዲስ አበባ፡- የመረጃ ነፃነትን ሊያስጠብቅ የሚችል እና መረጃን በአስር ቀናት ውስጥ ለመስጠት የሚያስገድድ አዲስ ረቂቅ አዋጅ መዘጋጀቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስታወቀ፡፡

የሕዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋም ዋና ዕምባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ኃይሌ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደተናገሩት፤ ቀደም ሲል መረጃ አልሰጥም

መረጃን በ10 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




















" በፍትሕ አሰጣጥ ዙሪያ በርካታ የማሻሻያ ሥራዎች ቢሠሩም አሁንም ያልተሻገርናቸው ሰፊ ችግሮች አሉ"

- አምባሳደር ደግፌ ቡላ
የፌዴራል ፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

ገጽ 3

ዜና

# በውጭ ሃገር የሚኖሩ ዜጎች ወደሀገራቸው ገንዘብ ሲልኩ ሕጋዊ መንገድን በመከተል ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ ቀረበ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከጥቁር ገበያ የሚያገኙትን ጥቅም በመተው ገንዘባቸውን በሕጋዊ መንገድ ወደሀገር ውስጥ በመላክ ለዘላቂ የሀገርን ግንባታ የበኩላቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ ጥሪ ቀረበ።

ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ ዲያስፖራና በአሜሪካ ካሮላይና ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ነጃት አብዱረህማን እንደተናገሩት፤ ዲያስፖራዎች በሚኖሩባቸው ሀገራት የሚያገኙትን ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ ብቻ ወደሃገራቸው በመላክ ለሀገር ግንባታ የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ ማሳደግ አለባቸው።

ገንዘባቸውን በሕጋዊ መንገድ ሲልኩ ዛሬ በጥቁር ገበያ የሚያገኙትን ትንሽ ጥቅም ሊያጡ እንደሚችሉ ወይዘሮ ነጃት ጠቁመው፤ ነገር ግን በሕጋዊ መንገዱ ገንዘባቸውን ሲልኩ የትውልድ ሀገራቸውን የኢኮኖሚ ግንባታ ማገዝ ይችላሉ ብለዋል።

ለትንሽ የገንዘብ ልዩነት ብለን በጥቁር ገበያ የመነዘርነው ገንዘብ ነገ ለሀገር ጠላት በሆኑ አካላት እጅ ይገባል፤ በመሆኑም በእራሳችን ገንዘብ ሀገራችንን የምናስወጋበት መንገድ ሰፊ ስለሚሆን ሕጋዊውን መንገድ መጠቀም ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የጥቁር ገበያን በመተው በሕጋዊ መንገድ ሲጠቀሙ ቋሚውን የሀገርን ግንባታ በአግባቡ እየደገፉ መሆኑን በይበልጥ ልንገነዘብ ይገባል ሲሉ ወይዘሮ ነጃት ተናግረዋል።

በአሜሪካ ዱክ ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽን ሲስተም ላብ ዳይሬክተር የሆኑት ወይዘሮ ኑሪያ አደም በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በሕጋዊ መንገድ የሚላከው ገንዘብ ከጥቁር ገበያው በተሻለ ሁኔታ ለሀገር ልማት የሚውል ነው።

የሀገር ልማቱን በመደገፍ ደግሞ ለአብዛኛው ዜጋ የጋራ ለውጥ የሚያግዙ ሥራዎች ማከናወን ይቻላል። በመሆኑም ዲያስፖራው በሕጋዊ መንገድ ገንዘብን በመላክ በጋራ ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ ሥራዎችን መደገፍ ይገባዋል ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል።

በጥቁር ገበያ የተላከውና የሚሸጠው ገንዘብ ዛሬ ላይ ትንሽ ጥቅም ሊያመጣ ይችላል፣ ነገር ግን የሀገርን ዘላቂ ሰላምና ልማት ለማኮላሸት የሚውሉ እኩይ ተግባራት ላይ እንደሚውል ማወቅ ይገባል ሲሉ ወይዘሮ ኑሪያ ተናግረዋል።

በመሆኑም የዲያስፖራው ማኅበረሰብ የዛሬውን ትንሽ ጥቅም ሳይሆን የአገሩን ጥቅምና የነገውን የሀገር ግንባታ በማሰብ ገንዘቡን ሲልክ ሕጋዊ መንገዶችን ሁሉ መጠቀም ይገባዋል ብለዋል።

ወይዘሮ ኑሪያ አክለውም፣ በመንግሥትም በኩል መሬት ላይ ያለውን ችግር ለማስተካከል በጥቁር ገበያ ችግሮች ላይ በሁሉም ዜጋ ላይ በአግባቡ ተፈፃሚ የሚሆን የሕግ አተገባበር ሊኖረው እንደሚገባ ጠቁመዋል።



ነጃት አብዱራህማን



ወይዘሮ ኑሪያ አደም



ጸጋ መድሕን

ከአሜሪካ የመጡት የፒርል ሊደርሽፕ ኢንስቲትዩት መሥራችና ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ጸጋ መድህን በበኩላቸው፤ ዲያስፖራው በዕውቀትና ክህሎቱ ሠርቶ የሚያገኘውን ገንዘብ በየትኛውም መመዘኛ ለግላዊና ለሀገር የኢኮኖሚ ልማት እንዲውል ማድረግ እንጂ ለጥፋት ዓላማ እንዲውል መፍቀድ የለባቸውም።

ለጥቁር ገበያ ሲሳይ የምናውለው ገንዘብ መንግሥትንና የሀገር ልማትን ተገዳዳሪ ጠላቶችን ዓላማ ማስፈጸሚያ እንደሚሆን ማወቅ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል። ፡

ወይዘሮ ጸጋ እንዳስታወቁት፤ ለተወሰነች የጥቅም ልዩነት በሚል ሀገርን ከመጉዳት ይልቅ በበዓላት ወቅትም ሆነ በሌሎች ጊዜያት ዲያስፖራው ወደኢትዮጵያ የሚልከውን ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል።



# ኢትዮጵያ እና ሱማሊያ የትራንስፖርት ዘርፉን ለማሻሻል የሁለትዮሽ ስምምነት ተፈራረሙ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ከሱማሊያ ሪፐብሊክ መንግሥት ትራንስፖርት እና ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ጋር የትራስፖርት ዘርፉን ለማሻሻል የሚያስችል የሁለትዮሽ ስምምነት ተፈራረሙ። ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት እንደሚያጠናክርም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ዳይሬክተር ጀኔራል አቶ ጌታቸው መንግሥቴ ስምምነቱን በተፈራረሙበት ወቅት እንደገለጹት፤ ስምምነቱ ማናቸውንም የሶማሊያ አየር ማረፊያዎች መጠቀም የሚያስችል ነው።

ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነቶች በቱሪዝምና በንግድ ለማጠናከር በትራንስፖርቱ ዘርፍ የነበሩ የበረራ ውስንነቶችን ለመቅረፍ እንደሚያግዝም ገልጸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የሶማሊያ ሲቪል አቪዬሽን አቅምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስችል ስምምነት ነው ብለዋል።

ሁለቱ ሀገራት ከፖለቲካ ዲፕሎማሲ ባሻገር ኢትዮጵያ ወደ ሱማሊያ የምትልካቸውን ምርቶች በተፈለገበት ሁኔታ እንዲደርሱ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ትስስሩን ከወትሮ በተሻለ መልኩ ያጠናክራል ብለዋል።

የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስትር ዳግማዊት ሞገስ በበኩላቸው ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት እንደሚያጠናክር በመግለጽ፤ በሀገራቱ መካከል የተሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል ብለዋል።

ስምምነቱ እንደ እህትማማች ሀገር አብረን ለመነሳት ትልቅ ማሳያ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሯ፤ ከዚህ በፊት የነበሩንን ጥቂት የአየር መንገድ መዳረሻዎች ለማሳደግ እንደሚያስችል ተናግረዋል።

ስምምነቱ በተቀመጠበት አቅጣጫ ተግባራዊ እንዲሆን መንግሥታቸው አስፈላጊውን ሁሉ እንደሚያደርግ ተናግረው፤ የሁለቱ ሀገራት ስምምነት የ2063 አጀንዳን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚያግዝ አያይዘው ገልፀዋል ።

የሶማሊያ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት እና ሲቪል አቪዬሽን ሚኒስትር ፈርዶዋስ አስማን በበኩላቸው ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት በማጠናከር ሱማሊያ በትራንስፖርቱ ዘርፍ ከኢትዮጵያ ልምድ ለመቅሰም ያስችላታል ብለዋል። ስምምነቱ ግንኙነታችን ወደቀጣይ ምዕራፍ ለማሸጋገር ትልቅ አቅም እንደሚሆንም ተናግረዋል።

# የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት:-

## - 1 ሺ 647 አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ሥራ አስገብቷል
## - 6 ሺህ 819 ነባር ኢንተርፕራይዞች እንዲጠናከሩ አድርጓል
## - ለ40 ሺህ 667 ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል

**ሞገስ ተስፋ**

አዳማ:- ባለፉት ስድስት ወራት አንድ ሺ 647 አዳዲስ አምራች ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋሙና 6 ሺህ 819 ነባር ኢንተርፕራይዞች እንዲጠናከሩ በማድረግ በድምሩ ለ40 ሺህ 667 ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ገለጸ።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ከክልልና ከተማ አስተዳደር ኢንተርፕራይዝ ቢሮዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ትናንት በአዳማ ከተማ ገምግሟል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አለባቸው ንጉሴ የኢንተርፕራይዙ የግማሽ ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ በቀረበበት ወቅት እንደተናገሩት፣ በግማሽ በጀት ዓመቱ አንድ ሺ 647 አዳዲስ ኢንተርፕራይዞች ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን 6ሺህ 667 ነባር ኢንተርፕራይዞች እንዲጠናከሩ ተደርጓል፡፡

ኢንተርፕራይዝ ልማቱ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል በሚኒስትሮች ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 526/2015 በአዲስ ተዋቅሮ ወደ ሥራ መግባቱን ጠቁመው፣ ደንቡ ለተቋሙ አዲስ ኃላፊነቶችንና ከዚህ በፊት እንደ ችግር ይታዩ የነበሩትን በመቅረፍ ውጤታማ በሚያስችል መልኩ ተግባርና ኃላፊነቱን እንዲወጣ ማስተካከያ ተደርጓል ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ፣ እንደ አገር ከተቀመጡ ዋና ዋና ግቦች መካከል አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማደራጀት የማምረት አቅማቸውን እንዲያሳድጉ፣ ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጠር፣ የተኪ ምርቶችን ማሳደግ እንዲቻል የተቀመጠውን ግብ ማሳካት ነው። ባለፉት ስድስት ወራት የአመራርና የአስፈጻሚ አካላትን አቅም ለማሳደግ በተሠራው ሥራ 10 ሺ 324 ለሚሆኑ አስፈጻሚዎችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል።

እንደ ዶክተር አለባቸው ገለጻ፣ ኢንተርፕራይዞች አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር የሚሆን ብድር ለሥራ ማስኬጃ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። የካፒታል ውጤታማነትን የፋይናንስ አገልግሎትን ለማቅረብ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን የሚሆን ብር በባንኮች በኩል እንዲመቻች በማድረግ የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ እንዲችሉ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ዶክተር አለባቸው እንዳሉት፣ ከአመራሩና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ጥሩ መሻሻል አለ። ነገር ግን በፌደራልና በክልል ደረጃ መረጃን በሚገባ ተንትኖ በመያዝ በኩል ውስንነቶች አሉ፣ ከፋይናንስና ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ የቅንጅት ሥራ የላላ ነው። በቀጣይ በትኩረት በመቅረፍ አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም ወደ ሥራ በማስገባት ተኪ ምርቶችን ለማምረት ይሠራል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ባለፉት ስድስት ወራት ባከናወናቸው ሥራዎችም ለ40 ሺህ 667 ዜጎች የሥራ እድል እንደፈጠረም ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡



ዶክተር አለባቸው ንጉሴ

# “በፍትሕ አሰጣጥ ዙሪያ በርካታ የማሻሻያ ሥራዎች ቢሠሩም አሁንም ያልተሻገርናቸው ሰፊ ችግሮች አሉ”

- አምባሳደር ደግፌ ቡላ
የፌዴራል ፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በፍትሕ አሰጣጥ ዙሪያ በፍትሕ ተቋማት ላይ ለዘመናት ሲነሳ የነበረውን ቅሬታ ለመፍታት በርካታ የማሻሻያ ሥራዎች ቢሠሩም አሁንም ያልተሻገርናቸው ሰፊ ችግሮች መኖራቸውን በሚኒስትር ማዕረግ የፌዴራል ፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ደግፌ ቡላ አመለከቱ።

በአገሪቱ ፍትሕ ተቋማት በዓመት ከሚቀርቡት ከ 7 ነጥብ 4 ሚሊዮን ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ የሚያገኙት 2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብቻ መሆናቸውን በጥናት መመላከቱንም ጠቁመዋል።

አምባሳደር ደግፌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ባለፉት 30 ዓመታት የፍትሕ ተቋማት ገለልተኝነት አደጋ ላይ ወድቆ ዜጎች በተለይ በማረሚያ ቤቶች የሰብዓዊ መብት ጥሰት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነበር። የተጠያቂነት ሥርዓትም ላልቶ ሙስናና ሌብነት ብሎም የመልካም አስተዳደር ችግሮች በአገሪቱ ነግሰው ነበር።

ከለውጡ ወዲህ የለውጥ አመራሩ ያለ ፍትሕና የሕግ የበላይነት የሀገርን ሕልውናና የዜጎችን የመኖር ዋስትና ማረጋገጥ ስለማይቻል ለፍትሕ ተቋማት ሪፎርም ትኩረት በመስጠቱ በርካታ ለውጦች ተመዝግበዋል ያሉት አቶ ደግፌ፤ አደናቃፊ የሆኑ ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም አሠራሮች እንዲሻሻሉ ተደርገዋል ብለዋል።

ሆኖም ግን ለውጡ በተፈለገው ልክ ውጤታማ እንዳይሆን ያልተቀረፉ በርካታ እንቅፋቶች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በተለይ አንዳንድ የፍትሕ አካላት የራስ ጥቅም በማስቀደም ገለልተኛ ያለመሆን ችግር፣ የብቃት ውስንነትና የአመለካከት ችግር ዋነኛ እንቅፋቶች እንደነበሩ ጠቁመዋል።



አገልግሎት ላይ ያሉት የፍትሕ ብሔርና የወንጀል መቅጫ ሕጎችም ባለፉት 50 ዓመታት ያገለገሉና የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘቡ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በአጠቃላይ ችግሮቹ ለሪፎርሙ ውጤታማነት ደንቃራ መሆናቸውን አብራርተዋል።

በተጨማሪም ካለመናበብ፣ በመዋቅራዊና በውስጥ አሠራር ችግሮች፣በአመራሮች የብቃት ችግር፣ ሙብትና ግዴታን እንዲሁም ተግባርና ኃላፊነትን በውል ያለማወቅ ችግሮች ተደምረው በዜጎች ላይ የፍትሕ መጓደል የሚፈጸምበት ጊዜ መኖሩን ያነሱት አምባሳደር ደግፌ፤ ከዚህ አንጻር በተለይ በማረሚያ ቤቶች አካባቢ አንዳንድ ጊዜ አንድ ተጠርጣሪ በፍርድ ቤት ነጻ ተብሎ ሲወሰን ፖሊስ በተጓዳኝ የሚያስርበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመዋል።

ፍትሕ በሀገሪቱ እንዲሰፍን በፍትሕ ተቋማት የሪፎርም ሥራዎች ከሌሎች ተቋማት በተለየ መልኩ ማድረግ የተፈለገበት ዋና ምክንያት የፍትሕ ሥርዓቱ ከተዛነፈ የሰላም፣የልማትና የዴሞክራሲ ሕልውና አደጋ ላይ መውደቅ ብቻ ሳይሆን የመኖር ዋስትና ራሱ አይታሰብም ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል ከተከሰተው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ ከሰው ሕይወት መጥፋትና ከንብረት ውድመት ጀምሮ ከባባድ ወንጀሎች መፈጸማቸው መንግሥት በተደጋጋሚ ሲገልጽ መቆየቱን ያወሱት አምባሳደሩ፤ ሰላማዊ አየር ለማስፈን ጎን ለጎን በሙስና ላይ የተጀመረው የተጠያቂነት ሥርዓት በሁሉም ወንጀሎች የማስፈን ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ወንጀል ሠርቶ የሚደበቁበት ቦታ እንዳይኖር ካልተደረገ ወንጀል ለመሥራት የሚነሳሱ ሰዎች ወደኋላ ስለማይመለሱ ከቀውስ አዙሪት ማውጣት አይቻልም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሕዝቡም ወንጀለኞችን አሳልፎ የመስጠት ባሕል ማዳበር እንዳለበት አሳስበዋል።

ኢንስቲትዩቱም፣ ከአቅም ክፍተት ጋር ተያይዞ የሚፈጠር የፍትሕ መጓደል ለመግታት የአቅም ክፍተት በመለየት ለፍትሕ አካላት ሥልጠና እየሰጠ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመው፤ የሪፎርም ሥራዎችም ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ውጭም ሕጎች እንዲሻሻሉ ድጋፍ ከማድረግ በዘለለ ወንጀለኞችን በሕግ ለማቅረብ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የራሱን አስተዋፅዖ እያደረገ መሆኑንም አምባሳደር ደግፌ ጠቅሰዋል።

# ምዕመኑ ለቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት ድጋፍ እንዲያደርግ ተጠየቀ

## - ለመጀመሪያው ዙር ዕድሳት 272 ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ከ90 ዓመታት በላይ ላስቆጠረው የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ዕድሳት ምዕመኑ ድጋፍ እንዲያደርግ ተጠየቀ።

የካቴድራሉ አስተዳዳሪ ክቡር ሊቀ ሥልጣናት ቆሞስ አባ ሲራክ አድማሱ በትናንትናው ዕለት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በዕድሜ ርዝመት ምክንያት የመንበረ ፀባዖት ቅድሥት ሥላሴ ካቴድራል ጣሪያ እያፈሰሰ እና ግድግዳው እየፈረሰ ይገኛል።

በመሆኑም ይህ የሀገር ቅርስ ቅርስነቱን እንደተጠበቀ እንዲታደስ በሚመለከታቸው አካላት ጥናት የተደረገ ሲሆን በዚህ መሠረት ዕድሳቱ ተጀምሯል። ዕድሳቱም በሁለት ምዕራፎች የሚከናወን ይሆናል፡፡

የመጀመሪያው ዙር ዕድሳት የካቴድራሉ ሕንፃ ላይ ያተኮረ ዕድሳት ነው ያሉት አባ ሲራክ፤ ለመጀመሪያው ምዕራፍ ዕድሳት ብቻ 172 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የተለያዩ አካላት ለዕድሳቱ ድጋፍ እያደረጉ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን የጠቆሙት የቤተክርስቲያኑ ኃላፊ ምዕመኑ ለዚህ ታሪካዊ ቅርስ ዕድሳት የበኩሉን እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

ሃይማኖታዊም ሆነ ተፈጥሮአዊ ቅርሶችን መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ በመጠቆምም ቅርሶች ለሀገራዊ ልማት የሚውሉና ለመጪው ትውልድ የሚተላለፉ ተተኪ የሌላቸው እሴቶቻችን ናቸው ብለዋል፡፡ በመሆኑም ከነዚህ ሃይማኖታዊ ቅርሶች መካከል አንዱ የሆነውን የመንበረ ፀባዖት ቅድሥት ሥላሴ ካቴድራልን በመንከባከብ ምዕመኑ ቅርሱን ከአደጋ ሊጠብቅ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡


ፎቶ - በሐዱሽ አብርሃ

ክቡር ሊቀ ሥልጣናት ቆሞስ አባ ሲራክ አድማሱ

የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የመሠረት ድንጋይ ከተቀመጠበት ጊዜ አንስቶ ላለፉት 90 ዓመታት ቅርሱን በዘላቂነት ሊያቆይ የሚችል ጠንካራ እና ሁለንተናዊ ዕድሳት እንዳልተደረገለት ጠቅሰው፤ በዚህም ምክንያት የሕንፃው ጣራ እያፈሰሰ፣ ግድግዳው እየፈረሰ የተለያዩ ጉዳቶች እየደረሱበት ስለሚገኝ ዕድሳቱ በታሰበለት ጊዜ እንዲከናወን ርብርብ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ጥቂት ጊዜ ከቆየ ካቴድራሉን እስከ ማጣት የሚያደርስ ጉዳት ይከሰታል ያሉት ኃላፊው፤ በመሆኑም በሲኖዶሱ እንዲሁም በቅርስና ጥበቃ ባለስልጣን እገዛ በቅርስ ዕድሳት ጥገና ሙያተኞች ተገቢው ጥናት ተደርጎ ዕድሳቱ መጀመሩን ተናግረዋል፡፡

የካቴድራሉን ሕንጻ ጥገናና ዕድሳት ቅድሚያ እንዲሰጠው ተደርጎ መጀመሩንና ይህም ጥገናና ዕድሳት ሥራ ከተቋራጩ ጋር በብር 172 ሚሊዮን ብር ውል ተፈርሞ ሥራው መጀመሩን አብራርተዋል፡፡

የካቴድራሉ ጥገና የሚያስፈልገው ሕንፃ ቤተክርስቲያኑ ብቻ ሳይሆን ምድረ ግቢውንም እንደሆነ በመጠቆምም፤ ምድረ ግቢውን የማስዋብና ያሉትንም መካነ መቃብራት ባሉበት ሁኔታ ጽዱና ተጎብኚ እንዲሆኑ ለማስቻል በጥናት ላይ ተመርኩዞ እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡

በቀጣይ የምድረ ግቢ ማስዋብ ሥራ ጥናት እንደተጠናቀቀና የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን ሲታወቅ ይፋ እንደሚደረግ እና በአሁኑ ሰዓት እየተደረገ የሚገኘው የዋናው ሕንጻ ቤተክርስቲያን ዕድሳት በተጀመረበት አግባብ እንደሚቀጥል አስረድተዋል፡፡

እስካሁንም የሕንጻው የምድር ቤት የመዋቅር ማጠናከር ሥራ እየተካሄደና በደውል ቤቶቹ ባለው ጉልላት ላይ ያለው መስቀል በማውረድ የጥገና ሥራው እየተከናወነ መሆኑን አክለው አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት እየተደረገ ባለው ዕድሳት በሕንጻው ውስጣዊ ክፍልና ውጫዊ ግድግዳዎች ላይ የመወጣጫና የድጋፍ ብረቶች መገጠማቸውንና በውስጥ የሚገኙ ሥዕላትና ሌሎች በጥገና ወቅት ጉዳት እንዳይደርስባቸው የአቧራና የግጭት መከላከያ ተደርጎላቸው ሥራው እየተከናወነ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡



አቶ ንጉሱ ጥላሁን

# በኤግዚቢሽኑ 600 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የ18 ሚሊዮን ብር ተጠቃሚ ይሆናሉ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በሀዋሳ ከተማ በሚካሄደው ኤግዚቢሽን በሚፈጠር የገበያ ትስስር 600 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የ18 ሚሊዮን ብር ተጠቃሚ ለማድረግ መታቀዱን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን በትናንትናው ዕለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤በሃዋሳ ከተማ ከጥር አራት እስከ ዘጠኝ ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለተመለመሉ ኢንተርፕራይዞች በሚካሄደው ኤግዚቢሽን ከዚህ በፊት ከተካሄዱት ኤግዚቢሽንና ባዛሮች በተለየ መልኩ በክላስተር ደረጃ ለማሳተፍና ለ600 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር በመፍጠር የ18 ሚሊዮን ብር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከተደራጀ ጊዜ ጀምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄድ ኤግዚቢሽንና ባዛር እንቅስቃሴ ሲሆን፤ ፕሮግራሙ ኢንተርፕራይዞች ችግር ሳይገጥማቸው በቀላሉ ምርትና አገልግሎታቸውን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም ኤግዚቢሽንና ባዛሩ ‹‹በሀገሬ ምርት እኮራለሁ፣ ከሀገር ውስጥ አምራቾች እገዛለሁ›› በሚል መሪ ቃል የሚካሄድ ሲሆን በሀዋሳ ከተማ ከጥር አራት እስከ ዘጠኝ እየተከበረ ይቆያል፤ 35 ሺህ ማኅበረሰቦች ይጎበኙታል ተብሎም ይጠበቃል ብለዋል፡፡

ከመንግሥታዊ ድጋፎች ውስጥ ኢንተርፕራይዞች ወደ ሥራ ከገቡ በኋላ አገልግሎትና ምርታቸውን የሚያቀርቡበት የገበያ ትስስር መፍጠር አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የሀገር ውስጥ ምርቶች ጥራትና ብቃት ኖሯቸው ቢመረቱም ኅብረተሰቡ ምርቶችን የመጠቀም ፍላጎቱ አነስተኛ ነው ያሉት አቶ ንጉሡ፤ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ኤግዚቢሽንና ባዛር ለማካሄድ ማቀዱ ለኢንተርፕራይዞች የምርታቸውን ጥራት፣ ብቃት፣ የአመራረት ቅልጥፍና የምርቶቻቸውን ጠቀሜታ ለማስተዋወቅና ኅብረተሰቡ የሀገር ውስጥ ምርቶችን እንዲያውቅና እንዲጠቀም ለማድረግ ያግዛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ባዛሩ 50 በመቶ ለሚሆኑ ሴት ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ ዕድል የሚፈጥርና አካል ጉዳተኞችንም ያካተተ እንደሚሆን የገለጹት ሚኒስቴር ዴኤታው፤ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢንተርፕራይዞችን አቅም ለማዳበር፣ ለማነቃቃት እንዲሁም የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ጥናትና የፓናል ውይይት እንደሚደረግ አመላክተዋል፡፡

ኤግዚቢሽንና ባዛሩ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ በግብር ሚኒስቴርና በሲዳማ ክልላዊ መንግሥት የሥራና ክህሎት ልማት ቢሮ ትብብር የሚካሄድ ነው፡፡ በፕሮግራሙ በአጠቃላይ በሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞች ከመላ ሀገሪቱ ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት በተለያዩ አካባቢዎች ኤግዚቢሽንና ባዛሮችን በማካሄድ ኢንተርፕራይዞችን የማነቃቃት፣ እርስ በርስ የማስተዋወቅና የማስተሳሰር ብሎም የገበያ ልምድ እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ ሲከናወን መቆየቱን ከሚኒስቴሩ የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

# ባለስልጣኑ ባለፉት ስድስት ወራት አንድ ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የአገልግሎት ገቢ ሰበሰበ

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት 665ሺህ 742 ተገልጋዮችን በማስተናገድ አንድ ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የአገልግሎት ገቢ መሰብሰቡን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ኃላፊ አቶ መስፍን መንግሥቱ እንደተናገሩት፤ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ባለፉት ስድስት ወራት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ከእነዚህም መካከል፤ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ መደገፍና የቢሮ አደረጃጀቱን ለተገልጋይ ምቹ ማድረግ ችሏል፡፡ በዚህም በቀን በአማካይ እስከ 10ሺ ያህል ተገልጋዮችን በማስተናገድ ባለፉት ስድስት ወራት አንድ ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የአገልግሎት ገቢ ሰብስቧል፡፡

በከተማው ካሉ ተቋማት መካከል ባለሥልጣኑ ከፍተኛ የተገልጋይ ቁጥር በማስተናገድ ተጠቃሽ መሆኑን ገልጸው፤ባለፉት ስድስት ወራት የአሽከርካሪነት ብቃት የማረጋገጥና ፈቃድ በመስጠት ውጤታማ ሥራ መሠራቱን ጠቅሰዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት 31ሺህ 913 ብቃታቸው ለተረጋገጠ ዕጩ አሽከርካሪዎች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠቱን ኃላፊው ተናግረዋል። የተግባር ፈተና በቀን የመፈተን አቅም ቀድሞ ከነበረበት እጩ ተፈታኝ ቁጥር ከ180 ወደ 400 አድጓል ብለዋል።



አቶ መስፍን መንግሥቱ

ለ424 ሺህ 590 ተገልጋዮች በተሽከርካሪ ዘርፍ አገልግሎት መሰጠቱን ጠቁመው፤ ከእነዚህ ውስጥ ለ18ሺህ 538 አዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ መደረጉን እና 20ሺህ 280 ተሽከርካሪዎች መደበኛ ሰሌዳ መስጠት መቻሉን ተናግረዋል፡፡

አገልግሎቱን በቴክኖሎጂ የታገዘ በማድረግ ረገድ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ፈተናን ሙሉ ለሙሉ በሲሲ ቲቪ ካሜራ የተደገፈ እንዲሆን መደረጉን አመልክተው፣ ከሰው ንኪኪ ነፃ በመደረጉም ቅሬታ ሲኖር በቪዲዮ የታገዘ የአፈታት ሥርዓት መዘርጋቱና ለተገልጋዮችም ፈጣን መስተግዶ መስጠት መቻሉን አብራርተዋል፡፡

ዕጩ አሽከርካሪዎች የተግባር ፈተና ውጤታቸውን በቴክኖሎጂ ታግዘው በ30 ደቂቃ ማየት መቻላቸው፣በአጭር መልዕክት በእጅ ስልክ ላይ የቀጠሮ ቀን ማወቅ መቻሉ የአገልግሎት አሰጣጡን እጅግ ዘመናዊ እንዳደረገው ተጠቁሟል።

## በጦርነት ውስጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ ዮሐንስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጦርነት ማግስት በአንድ ጊዜ ወደትምህርት አይገባም፤ ተማሪዎች፣ መምህራንና የአካባቢው ማኅበረሰብ ከደረሰባቸው ጉዳት እንዲያገግሙ የስነልቦና ጉዳት የማከም ሥራ ቅድሚያ ተሰጥቶት እየተሠራ ነው።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ ትምህርት ቤቶችን ለመክፈት የሚያስችል የአደረጃጀት ሥራዎችን የማጠናከር ሥራ እየሠራ የሚገኘው ቡድን በአካባቢው የቀረበውን የትምህርት ግብዓት ስርጭት የማፋጠን ሥራ እየሠራ ይገኛል። ትግበራውም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ትምህርት ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ከሚመራው የስትሪንግ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ትምህርት ለማስጀመር በግጭቱ የደረሱ ጉዳቶች በትምህርት ዘርፉ ያመጡትን አሉታዊ ነገር መረጃ የማሰባሰብ ሥራ እየሠራ መሆኑን አመልክተዋል። መረጃውን መሠረት በማድረግም የፈጣን ምላሽ እቅድ እንደሚሰጥም ነው የጠቆሙት።

ትምህርት ባልተጀመረባቸው የትግራይ ክልል አካባቢዎች የተለያዩ የመሠረተ ልማት ግብዓቶችን በማቅረብ በቅርብ ጊዜያት ትምህርት እንደሚጀመርም ተናግረዋል። በአማራ ክልል ትምህርት ባልተጀመረበት በዋግ ኽምራ ዞን የተወሰኑ አካባቢዎች በቅርቡ ትምህርት እንደሚጀመርም ጠቁመዋል።

የጸጥታ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ይገኛል ያሉት አቶ ዮሐንስ፤አፋር ክልል ዞን ሁለት አካባቢ ከ80 በመቶ በላይ ትምህርት የተጀመረው ከደረሰባቸው ጉዳት እንዲያገግሙ የማከም ሥራ ከተሠራ በኋላ መሆኑንም ነው የገለጹት።

ሁሉም ባለድርሻዎች በመልሶ ማልማት አስተዋፅዖና ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የሚያስፈልገውን በጀትና የሰው ኃይል ከፍተኛ በመሆኑ መላው ኅብረተሰብ በሚመለከተው ፈርጅ ውስጥ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

በጦርነቱ ምክንያት የፈረሱ አደረጃጀቶችን መልሶ የሚያጠናክር ትግራይ፣ አፋርና አማራ ክልሎች ላይ አራት ቡድን ተደራጅቶ ሥራ ተጀምሯል። የአፋር አብአላን መሠረት አድርጎ ዞን ሁለት በተባለው አካባቢ ላይ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ያሉበትን ደረጃ በመለየት አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ ይደረጋል።

በተመሳሳይም በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደርን ማዕከል አድርጎ በአካባቢው ያሉ ሁኔታዎችን በማጥናት የትምህርት ሥርዓት መልሶ እንዲደራጅ ያደርጋል። በትግራይ ደግሞ ሽሬ፣አድዋና አክሱም አካባቢዎችን ማዕከል አድርገው የሚሠሩ ሁለት ቡድኖች ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ።

ከኅብረተሰቡ ጋር መወያየት፣ በትምህርት ዘርፍ መዋቅር ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ባለሙያዎች እና አመራሮችን ማንቀሳቀስ እና ከባለሙያዎቹ ጋር የጋራ ግንዛቤ መውሰድ፣ ትምህርት ቤቶች ያሉበትን ደረጃ ማየት፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየትና ትምህርትን በፍጥነት ለማስጀመር የሚያስችሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመቃኘት እየተሠራ ነው።

ቡድኑ ሲመለስ የትምህርት ዘርፍ ምላሽ ከአደረጃጀት፣ ከግብዓት እና ከሌሎች መሠረተ ልማት አንጻር ቀጣይ ሥራ እንደሚሠራም አቶ ዮሐንስ አመልክተዋል።

## መረጃን በ10 ቀናት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያሉትን ለመክሰስ፤ ከ90 እስከ 120 ቀናት መጠበቅ የግድ የነበረ ሲሆን በአዲሱ ረቂቅ አዋጅ ግን በ10 ቀናት ውስጥ ለመረጃ ፈላጊው ምላሽ እንዲሰጥ አስገዳጅ ሕግ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በረቂቅ አዋጁ መሠረት አንድ መረጃ የፈለገ መገናኛ ብዙኃን ወይም ግለሰብ በ10 ቀናት ውስጥ የሚፈልገውን መረጃ ማግኘት እንዳለበትና ካልሆነ ግን ክስ የሚያቀርብበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመዋል፡፡

እስካሁን ድረስ መረጃ በሚከለክሉ ተቋማት የሚያስጠይቅ ሕግ የለንም ነበር ያሉት ዶክተር እንዳለ በተቃራኒው ግን በአዋጅ 590/2000 አንድ ሚዲያ ያልሆነ ነገር አስተላልፎ ቢገኝ በገንዘብም በእሥራትም የሚቀጣ መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል ይላሉ።

የሕግ ማዕቀፍ ባይኖርም ግን ተቋሙ መረጃ መከልከልን እንደ አንድ አስተዳደራዊ በደል በመውሰድ በአዋጅ ቁጥር 1142/2011 ተጠያቂ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን አብራርተዋል። እስካሁንም ድረስ ይህንን ያደረጉ አገልግሎት ሰጪዎችን በሚዲያ ከማጋለጥ አንስቶ ክስ እስከመመሥረት ድረስ የሚደርስ ሥራ ሲሠራ መቆየቱን ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ ቁጥር 1142/2011 እና የመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 የሕዝብን አቤቱታ ተቀብሎ አስፈፃሚ አካላትን የመጠየቅ ተግባርና ኃላፊነት እንዳለው ዶክተር እንዳለ ተናግረዋል፡፡

## ኢትዮጵያና ቻይና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሚኒስትሩ በቅርብ ጊዜ የተሾሙ በመሆናቸው መጪው ጊዜ የተሳካ እንዲሆንላቸውም ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተሾሙ ማግስት ወደ አፍሪካ በሚያደርጉት ጉብኝት ኢትዮጵያን መነሻ በማድረጋቸውም ምስጋና አቅርበዋል፡፡ ቻይና በዓለም አቀፍ መድረክ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ጽኑ አቋም በመያዝ ያላትን ተከታታይና በመርሕ ላይ የተመሠረተ አቋምም አወድሰዋል፡፡

አቶ ደመቀ፤ የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነትና የትግበራ ሁኔታም በተመለከተ ከቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር መወያየታቸውን ጠቅሰው ቻይና ለኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት የምታደርገውን ድጋፍ አድንቀዋል፡፡

ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች በትብብር እየሠራች ያለች በመሆኗ ይህንን ትብብር አጠናክራ ድጋፏን እንድትቀጥል፣ የቻይና ኩባንያዎች በኢንቨስትመንት መስክ እንዲሠማሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቺን ጋንግ በበኩላቸው፤ ላለፉት በርካታ ዓመታት የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች አፍሪካን የመጎብኘታቸው ሁኔታ ቻይና ከአፍሪካ ጋር ያላትን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡

ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ትብብር እንዳላት በመግለጽ፤ የኢትዮ-ቻይና መልካም ግንኙነትና ወዳጅነት በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ሁሉን አቀፍ ስትራቴጂካዊ ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያደርስ ተናግረዋል፡፡ በቀጣይም የኢትዮ-ቻይናን ሁለንተናዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ ትብብሩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ነው የተናገሩት፡፡

ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት የማይለዋወጥና በዘላቂ ትብብር ላይ የተመሠረተ እንደሆነ በመጠቆም፤ ታሪካዊ ግንኙነቱን ይበልጥ ለማጠናከር እንደሚሠሩ ገልጸዋል፡፡ ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር ባላት የሁለትዮሽ ግንኙነቷ፣ በቀጣናዊና በዓለም አቀፍ መድረኮች በትብብር መሥራቷን ትቀጥላለችም ብለዋል፡፡

የቻይና መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚስተዋለው የሁኔታዎች ተለዋዋጭነት አንጻር ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ሁለንተናዊ ወዳጅነት ለማጠናከርና ለማስቀጠል ቁርጠኛ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

የቻይና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዲሳተፉ የቻይና መንግሥት የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቅሰዋል፡፡ በፕሪቶሪያ የተደረገው የሰላም ስምምነት እንዳስደሰታቸውም በመግለጽ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለዚሁ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## "የተጀመረውን ሰላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረችው፤ የፌዴራል መንግሥትም ሆነ ሕወሓት የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ የወሰዱት የሰላም አማራጭ ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ነው፡፡ ለተግባራዊነቱም አስተዋፅዖ ያደረጉ አካላት ሁሉ መመስገን ይገባቸዋል፡፡

ሰላሙን ለማስቀጠል የሰላምን ውድ ዋጋ በመገንዘብ ሰላሙን ማፅናት ያስፈልጋል ያለችው ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ፤ እያንዳንዱ ዜጋ የተገኘውን ሰላም ለማፅናት መረባረብ አለበት ብላለች፡፡

ስለ ሰላሙ ሁኔታ እንደ እህትም እንደ እናትም ስንጨነቅ ነበር ያለችው ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ፤ ጭንቀታችን ተሰምቶ ሰላሙ በመመለሱ ደስተኞች ነንም ነው ያለችው፡፡ ሰላምን በሚመለከት ሕዝብ ጥያቄ እንዳይኖረው የተጀመረውን የሰላም ጉዞ ማፅናት ያስፈልጋልም ስትል ተናግራለች፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ሰላም ምንም አይነት ጥርጣሬ እንዳይኖረው ለዘላቂ ሰላም የሚያስፈልጉ ማናቸውንም የቤት ሥራዎች ማከናወን እንደሚያስፈልግ የገለጸችው ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ፤ ሰላም የሁሉንም ጥረት የሚፈልግ በመሆኑ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የየራሱን አስተዋፅዖ እንዲያበረክትም ጥሪዋን አስተላልፋለች፡፡

በሰፈነው ሰላም ደስተኛ ነኝ ያለችው ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ፤ በመቀሌው ጉዞ ኢትዮጵያ እንኳን ሰላም ሰፈነባት፤ እንኳንም የተነፋፈቁ ሕዝቦች ተገናኙ በማለት የእንኳን ደስ ያለን መርሐግብር እንደሚኖርም ገልጻለች፡፡

ሰላም ካለ የተፈለገው ሁሉ ይሆናል፤ እኛም ወደ መቀሌ መጓዝ የቻልነው ሰላም በመኖሩ ነው ያለችው አትሌት ደራርቱ፤ ሁሉም ሰው የሰላምን ውድ ዋጋ በመረዳት ለዘላቂነቱ የየራሱን ሚና እንዲወጣም አሳስባለች፡፡

በመቀሌው ጉዞ የትግራይ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በምን መንገድ መደገፍ ይቻላል የሚለውን ምክክር በማድረግ በሙያ፣ በፋይናንስ እንዲሁም በቁሳቁስ እገዛ ለማድረግ ሥራዎች እንደሚሠሩም ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ አብራርታለች፡፡

ከቡድኑ አባላት አንዷ የሆነችው አትሌት ለተሰንበት ግደይ በበኩሏ ዛሬ የተሰማኝ ስሜት ሪከርዶችን ስሰብር ከተሰማኝ የደስታ ስሜት የሚልቅ ነው ስትል ተናግራለች፡፡

አትሌቷ እንደገለጸችው፤ በትላንቱ የመቀሌ ጉዞዋ የተሰማት ስሜት ከቃላት በላይ የሆነ ዓለም አቀፍ ሪከርዶችን ስትሰብር ከሚሰማት የሚልቅ የደስታ ስሜት ነው፡፡

የፌዴራል መንግሥትም ሆነ ሕወሓት ሰላምን ምርጫቸው በማድረጋቸው ደስተኛ ነኝ ያለችው አትሌት ለተሰንበት ለሰላሙ ዘላቂነትና ከዚህ በላይ ወደ አንድነት የሚደረገው ጉዞ ሊቀጥል የሚገባው መሆኑን መክራለች፡፡

አትሌት ለተሰንበት በአስር ሺህ ሜትር የዓለም ሻምፒዮና ለሀገሬ ወርቅ ሳመጣ የሮጥኩት ለሀገሬ፣ ለባንዲራዬ ክብር እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነውና ደስ ብሎኝ ነበር፤ ቢሆንም ያለ ቤተሰብ ሙሉ አልነበረምና ፈጣሪንም ምናለ አንድ ብታረገን ሰላም፣ ቢሆንልን ብዬ ተመኝቼ ነበር፤ አሁን ምኞቴ ተሳክቷል ብላለች፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት ዘመን የማይሽረውና ተምሳሌታዊ ነው!

የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት ከግማሽ ክፍለ ዘመናት በላይ የተሻገረ ነው፡፡ በእነዚህ ዓመታትም ሁለቱ ሀገራት የሕዝቦቻቸውን ጥቅም የሚያስከብሩ ተግባራት ከማከናወናቸውም ባሻገር የርስ በርስ መተሳሰብንና መተማመንን በማስቀደም ተምሳሌታዊ ግንኙነት መፍጠር ችለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የሚያጋጥሟትን ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመሻገር የምታደርገውን ጥረት በማገዝ ቻይና የበኩሏን እገዛ ስታደርግ ቆይታለች፡፡ ለአብነትም ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የሆነውን ኮቪድ 19 በመከላከሉ ረገድ ቻይና ያደረገችው ድጋፍ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ የቻይና መንግሥት ኢትዮጵያ እያካሄደች ላለችው የጸረ ኮቪድ 19 ዘመቻ ከ12 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶዝ በላይ ክትባት በመለገስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ወገንተኝነት ማሳየት ችሏል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ቻይና በኮቪድ ወረርሽኝ በተጠቃችበትና በዚሁ ምክንያትም መላው ዓለም ወደ ቻይና በረራ በሰረዘበት ወቅት በብቸኝነት በረራ በማድረግ በችግር ጊዜም ቢሆን የቻይናና ኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይለያዩ ያስመሰከረበት ታሪካዊ ሁነት መቼም የሚረሳ አይደለም፡፡ በወቅቱም የዓለም ሀገራት ወደ ቻይና በረራ ባቆሙበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት በብቸኝነት የወሰደው ጥንቃቄ የተሞላበት ርምጃ ከቻይና መንግሥትና ሕዝብ አድናቆት የተቸረው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፧

ኢትዮጵያ በየጊዜው የሚያጋጥሟትን ሰብዓዊ ቀውሶች በማቃለል ረገድም የቻይና መንግሥት ድጋፍ የማይነጥፍ ነው፡፡ በተለይም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ለተጎዱ ዜጎች የቻይና መንግሥት ከ30 ሚሊዮን የቻይና ዩዋን በላይ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ የምታከናውናቸውን የተለያዩ ልማቶችን በመደገፍም የቻይናን መንግሥት አበረታች አስተዋፅዖ በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የቅርቡን እንኳን ብንመለከት በአዲስ አበባ እየተከናወኑ የሚገኙትን የአረንጓዴ ልማትና አካባቢ ማስዋብ ሥራዎችን በመደገፍ ረገድ የቻይና መንግሥት የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ግዙፉ የንግድ ባንክ ሕንጻና የሳይንስ ሙዚየም ግንባታዎች የቻይናውያን አሻራ ያረፈባቸው ድንቅ የልማት ውጤቶች ናቸው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ 90 ሺህ ሜትር ስኩዌር የሚሸፍን ቦታ ላይ ዘመናዊ የሆነ የአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል ዋና መሥሪያ ቤት ተገንብቶ ለምረቃ የተቃረበውም በቻይና ድጋፍ ነው ።

ኢትዮጵያ በለውጥ ጎዳና ውስጥ በገባችባቸው ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥም ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሠረት እንዲጥልና የህዋ ምርምር እንዲዳብር ቻይና ያልተቆጠበ ድጋፍ አድርጋለች፡፡ የቻይና መንግሥት ከ250 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ በማድረግ ETRSS-1 እና ET-Smart-RSS የተሰኙ ሳተላይቶችን ኢትዮጵያ እንድታመጥቅ በማድረግ አጋርነቱን አሳይቷል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያ ሦስተኛዋን ሳተላይት ለማምጠቅ በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡

ከልማቱና ከሰብዓዊ ድጋፍ ባሻገር የቻይና መንግሥትና ሕዝብ በዓለም አቀፍ መድረክ ከኢትዮጵያ ጎን ተለይተው አያውቁም፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ተከስቶ የነበረውን ጦርነት ለግል ፍላጎታቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ለማዋል የሚፈልጉ ሀገራት ጉዳዩን ከሚፈለገው በላይ በማግዘፍ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ለ12 ጊዜያት ያህል እንዲታይ ሲያደርጉ በሁሉም መድረኮች ቻይና ከኢትዮጵያና ከእውነት ጎን በመቆሟ የተጎነጎኑትን ሴራዎች ለማክሸፍ ትልቅ አቅም ሆኗል፡፡

ዘመን የማይሽረው የኢትዮ-ቻይና ግንኙነት ዛሬ ወደ ላቀ ደረጃ ተሸጋግሯል፡፡ በቅርቡ የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ቺን ጋንግ በሥልጣን ዘመናቸው የመጀመሪያ የሆነውን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት በኢትዮጵያ በማድረግ የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት ዛሬም እንደትናንቱ በተጠናከረ መልኩ መቀጠሉን አረጋግጠዋል።

ይህንኑ ጉብኝት በተመለከተም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ "የቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቺን ጋንግ እንኳን ወደ ኢትዮጵያ በደኅና መጡ። የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት አሁንም ጸንቶ ቀጥሏል። የዛሬው ውይይታችን ይህንን እና በልማት የምንጋራውን ስልታዊ የጋራ ዓላማ፤ እንዲሁም አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ትብብርን አጉልቶ አሳይቷል" ሲሉ በይፋዊ የፌስ ቡክ ገጻቸው መልዕክት አስተላልፈዋል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# አገር የሚተዋወቅባቸው አጋጣሚዎች

**ሚሊዮን ሺበሺ**

‹‹ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች አገር ናት›› የሚለው አገላለጽ በጣም ስለተደጋገመ ምናልባትም አሰልቺ ይመስል ይሆናል። ምናልባትም ለአንዳንዶች ራሳችንን ለማካበድ የምንጠቀመው ወይም የተለመደ ተረት ተረት ይመስላቸው ይሆናል። ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች መሆኗን ለማሳየት ግን የሳይንስ ጥናትም ሆነ የፈላስፋ ጥቅስ መጥቀስ አያስፈልገውም። በየወቅቱ በዓለም መገናኛ ብዙኃን የምናየውና የምንሰማው ሀቅ ነው። የውጭ አገራትን የማየት ዕድል ያገኙ ደግሞ በዓይናቸው ያዩት ነው።

የሥልጣኔ ማማ ላይ ያሉ አገራት በከፍተኛ ሙቀት ወይም በከፍተኛ ብርድ ይጠቃሉ፤ በአየር ንብረት ምክንያት የበርካታ ሰዎች ሕይወት ያልፋል። በቅርቡ እንኳን በአሜሪካና የአውሮፓ አገራት ውስጥ ያየነው ይህንኑ ነው። ተሽከርካሪዎች ሥራ እስከማቆም የደረሱበት ሁኔታ ነበር። ለዚያውም እነዚህ የበለጸጉ አገራት አለ የሚባለውን የሙቀትም ሆነ የቅዝቃዜ መከላከያ የሚጠቀሙ ናቸው።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ የ13 ወር የፀሐይ ፀጋ ያላት አገር ናት። አልፎ አልፎ ሙቀትና ቅዝቃዜ ቢኖርም የሰው ሕይወት የሚቀጥፍና ተሽከርካሪን ሥራ የሚያስቆም ግን የለንም። በዚህ አየር ንብረት ምክንያት ብዙ አይነት የዕፅዋትና አዝርዕት አይነቶች አሉን። በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የእንስሳት አይነቶች አሉን። አስገራሚ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ቦታዎች አሉን። ታዲያ ይህን ድንቅ ተፈጥሮ፣ ውብ ባህልና ትውፊት ለዓለም የምናስተዋውቀው መቼ ነው?

ምንም እንኳን አገርን ለማስተዋወቅ የጊዜ ገደብ ባይኖረውም የታኅሣሥና ጥር ወራት ግን የበለጠ ምቹ ናቸው። ምክንያቱም የገና እና የጥምቀት በዓላት አሉን። ሁለቱም የዓለም ሕዝብ የሚመለከታቸው ናቸው። ገና የዓለም ሀብት በሆነው ላልይበላ ይከበራል። ጥምቀት ደግሞ አከባበሩ ራሱ የዓለም ሀብት ሆኗል።

እነዚህ በዓላት የሚከበሩት ከሚከበሩበት ቀን ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት እና የሚከበሩበት ቀን ካለፈም በኋላ ነው። ለምሳሌ ለገና የመጡ የውጭ አገራት እንግዶች የመጡት ቀደም ብለው ነው። አሁንም ይኖራሉ። የፊታችን ጥር 11 ለሚከበረው የጥምቀት በዓልም እንግዶች ከወዲሁ መግባት ይጀምራሉ።

የዘንድሮውን በዓላት ደግሞ ለየት የሚያደርጋቸው የዓለም መገናኛ ብዙኃን ሲያስፈራሩበት የቆየው የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት እልባት አግኝቶ ሰላም በሰፈነ ማግስት መሆኑ ነው። እግረ መንገዳቸውንም ‹‹ይህን የመሰለ ሰላም ያለበት አገር ነው እንዴ ጦርነት ነበረበት የተባለ!›› ብለው እንዲገረሙ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ሁነቱም ይሄንኑ ያደርጋል።

ምክንያቱም አገራችንን የምናስተዋውቃት በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ነው። ምናልባት ብዙዎቻችን ለውጭ ዜጎች አገርን ማስተዋወቅ የአስጎብኚዎች ሚና ብቻ ይመስለናል። ሆኖም በአገሩ ጉዳይ ማንም አስጎብኚ ነው። ለውጭ አገራት ዜጎች ተገቢውን መረጃ መስጠት የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

ይህን ለማለት የተገደድኩበት ምክንያት በብዙ ቦታዎች የምታዘበው ነገር ስላለ ነው። ባረፍንበት ቦታ፣ በገባንበት ካፌ፣ በምንጓዝበት ተሽከርካሪ ውስጥ እንዲሁም በዓላቱ በሚከበሩባቸው ቦታዎች ላይ የውጭ ዜጎችን እናያለን። ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ለእነዚህ የውጭ ዜጎች ያላቸው አቀባበልና መረጃ አሰጣጥ ልክ አይደለም።

እርግጥ ነው የቋንቋ ገደብ ይኖራል፤ ችግሩ ግን የቋንቋ ብቻ ሳይሆን የአመለካከትም ጭምር መሆኑ ነው። አንዳንዱ ልክ እንደ ኩራት በማየት ለነጭ አልለማመጥም አይነት ምልክት ያሳያል። ሆኖም እንግዳን መንከባከብ ፍርሃት ወይም ባርነት ሳይሆን ትህትና ነው። አዎ! በቅኝ ያልተገዛን፣ ወራሪን አሳፍረን የመለስን፣ የራሳችን ማንነት ያለን ነን። ይህን የምናሳየው ግን እንግዳ ሆኖ በመጣ አካል ላይ አይደለም።

እዚህ ላይ ባለፈው ዓመት የተከሰተ የአንድ ግለሰብ ገጠመኝ ልጥቀስ። ግለሰቡ ከአንዲት ሴት ጋር ካፌ ውስጥ ቁጭ ብሏል። ወደ መታጠቢያ ክፍል እንደሄደ አራት የውጭ ዜጎች ወደ ካፌው መጡ። ካፌው ውስጥ ያሉ ቦታዎች ተይዘው አራት ሰው መያዝ የሚችል ያለው እኚህ ሴትና ወንድ የተቀመጡበት ቦታ ብቻ ነው።

የካፌው ባለቤት ይሁን ሥራ አስኪያጅ በትህትና ወደ ልጅቷ ሄዶ ‹‹እናንተ ሁለት ስለሆናችሁ እዚያች ጋ ብትቀመጡ›› ብሎ ነገራት። ልጅቷም ተነስታ ሁለት ሰው ብቻ ወደሚይዘው ወንበር ሄደች። ልጁ ከመታጠቢያ ክፍል ሲመለስ ቦታ ቀይራለች። ‹‹ምነው?›› ሲላት የሆነውን ነገረችው። በፊት የተቀመጡበት ቦታ ላይ የውጭ ዜጎችን ሲያይ ያዙኝ ልቀቁኝ አለ። እንደ ዓድዋ ያሉ የታሪክ ድሎችን መዘርዘር ጀመረ። ‹‹ኧረ ባክህ ይሄ ከእርሱ ጋር አይገናኝም!›› ቢባል ሊሰማ አልቻለም። በመጨረሻም ካፌውን ለቆ ሄደ።

እስኪ ይህን ነገር በቅንነት እንየው! እንግዶቹ አራት ናቸው፤ እነዚህኞቹ ደግሞ ሁለት ናቸው። ታዲያ ቦታ ቢቀይሯቸው ምን ችግር አለው? በዚያ ላይ የውጭ ዜጎች አይደሉም ተነሱልን ያሉት፤ የካፌው ባለቤት ነው በትህትና የጠየቃቸው። በትህትና መጠየቁን ደግሞ ያዙኝ ልቀቁኝ ያለው ልጅ ራሱ አምኗል።

እንዲህ አይነት ስሜቶችን እንደ አገር ፍቅር አላያቸውም! እንዲያውም አገርን እንዴት ማስተዋወቅ እንዳለብን አለማወቃችንን ነው የሚያሳየው። አዎ! አገርን ለማስተዋወቅ ባሪያ እና አጎብዳጅ መሆን የለብንም፣ ለፈረንጅ መስገድ የለብንም፤ ዳሩ ግን አግባብ ባልሆነ ሁኔታ መፎከር ደግሞ ኋላቀርነትን እንጂ ሥልጣኔን ወይም ኩሩነትን አያሳይም።

አገርን ማስተዋወቅ ምርትና አገልግሎትን እንደማስተዋወቅ ነው። የሰዎች አዕምሮ ውስጥ መሥራት ነው። ማስተዋወቅ ደግሞ አወንታዊ ጎኖችን ለይቶ ማጉላት ማለት ነው። በለጸጉ በሚባሉ አገራትም እያየነው ያለነው ይህንኑ ነው። በፊልሞቻቸውና በባህላቸው ውስጣችን ገብተዋል። በፊልሞቿና ባህሏ የምንወዳት ሕንድ የድሃ ድሃ የሚባሉ ሕዝቦች ያሉባት ናት። በየዘጋቢ ፊልሞች እንደምናየው እጅግ አስደንጋጭ የሆነ የችግር ኑሮ የሚኖሩ ዜጎችም አሏት፤ ዳሩ ግን በሰራችው ራስን የማስተዋወቅ ሥራ ህንድ የምትታወቀው በዚህ አይደለም።

የዓለም ልዕለ ኃያል የምትባለው አሜሪካ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የጦር መሳሪያ የሚያዝባት ናት። በዚህ ሳምንት እንኳን አንድ የስድስት ዓመት ሕጻን መምህሩን በሽጉጥ አቁስሏል። ይህ በተደጋጋሚ የሚሰማ ሃቅ ነው። እንዲያውም የቀድሞ ፕሬዚዳንቷ ዶናልድ ትራምፕ መምህራኑን አስታጥቃለሁ ሲሉ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አሜሪካ የምትታወቀው የሥልጣኔ ጣሪያ በመሆኗ ነው።

እንዲህ ተፈጥሮ አድሎን፣ ሰው ሰራሽ ችግሮቻችን ግን ኋላቀር አድርገውናል። ስለዚህ ከእነዚህ ችግሮች እንላቀቅ። አገራችንን በበጎ እናስተዋውቅ። ለዚህ ደግሞ እንደ ገና፣ ጥምቀትና መስቀል የመሳሰሉ በዓላት ምቹ ናቸው። አገርን ማስተዋወቅ ሲባል ግን የግድ እነዚህን ቀናት ብቻ መጠበቅ አይደለም። ቀደም ሲል እንዳልኩት በየትኛውም አጋጣሚ ለምናገኛቸው እንግዶች ተገቢውን መረጃ መስጠት ነው።

በዚህ ረገድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ አንድ ልብ ያልኩት ነገር አለ። የውጭ ዜጋ የሆኑ መምህራን ገና ወደ ክፍል የገቡ ቀን የመጀመሪያ ሥራቸው ስለአገራቸው መናገር ነው። የአገራቸው ምርት የሆኑ ነገሮችን ከቦርሳ እያወጡ ይሰጡናል። በተለይም የአውሮፓ አገራትና የህንድ ዜጎች ይህን ነገር በሚገባ ይጠቀሙታል። እናም እኛ ኢትዮጵያውያን ቦታ እና ጊዜ ሳይገድበን ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ አገራችንን እናስተዋውቅ!

## ተጠየቅ

# ‹‹ኅብረተሰቡ የመልካም አስተዳደር ችግርን በመቃወም በመብቱ መገልገልን ቢለማመድ ሀገሪቱ እውነተኛ ዴሞክራሲ ይሰፍንባታል››

**- ዋና እንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ሀይሌ**



<u>አስመረት ብስራት</u>

**የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደል የደረሰባቸውን ዜጎች እንባ በማበስ ትክክለኛውን ፍትህ እንዲያገኙ የሚያደርግ ተቋም ነው። ባለፋት ረጅም ዓመታት በደል የደረሰባቸውን የበርካቶችንም እንባ አብሷል። ሆኖም ግን ይሄ በቂ አይደለም፤ ስልጣኑም ጥርስ የሌለው አንበሳ አይነት ነው የሚሉ ቅሬታዎች በብዛት ይደመጣል። ለዛሬ ‹‹የተጠየቅ አምዳችን›› እነዚህንና ሌሎች ሀሳቦችን በማንሳት የተቋሙን አጠቃላይ የስልጣን ደረጃ በመዳሰስ፤ መረጃን ለማይሰጡ ተቋማት እስከምን ድረስ ሄዶ መረጃ ያሰጣል ? የሚሉትን ጭምር በማንሳት ከኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ ከሆኑት ከዶክተር እንዳለ ሀይሌ ጋር ቆይታ አድርገናል።**

**አዲስ ዘመን፤ የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ስልጣንና ኃላፊነት ምንድነው?**

**ዶክተር እንዳለ፤** የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ተግባርና ሀላፊነት የሚነሳው ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት ነው። ሌላው በአዋጅ ቁጥር 1142/2011 እና የመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 ከእነዚህ ሁለት አዋጆች የሚመነጭ ስልጣንና ተግባራት አሉት። በሁለቱም አዋጆች መሰረት የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አብዛኛው የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የማይገነዘቡት ተቋሙ በህገ መንግስቱ እና ባወጧቸው ህጎች መሰረት መስራታቸውን የመከታተል ስልጣን አለው።

በዚህም መሰረት አስፈፃሚ አካላቱ ባወጧቸው ህጎች የማይገዙ ከሆነ፤ የአስተዳደር በደል ደርሶብናል ሲሉ የመጡ አካላት ካሉ፤ የመፍትሄ ሀሳብ የመስጠት ማለትም ህጉን መቀየር ወይም ማሻሻል ይችላሉ። እኛ ህግ አክብሩ የህግ የበላይነት እንዲከበር ስሩ በማለት አቅጣጫ እናሳያለን። ከዚህም በተጨማሪ አቤቱታ በመመርመር፣ በቁጥጥርና ክትትል እንዲሁም ጥናት በማድረግ ጭምር ግንዛቤ የማሳደግ ስራዎችን ተቋሙ ይሰራል።

**አዲስ ዘመን፤ አስተዳደራዊ በደል የደረሰባቸውን ግለሰቦች እንባ በማበስ ተቋሙ ምን እየሰራ ነው?**

**ዶክተር እንዳለ፤** የመንግስት አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸውን ህጎች፤ ደንቦችና መመሪያዎች ሰራተኛውም ሆነ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ብሎም ሌሎች ዜጎች በእነዛ ህጎችና ደንቦች ይገዛሉ። ህጉን ያወጣው አካልም በወጣው መመሪያ መሰረት አገልግሎት መስጠት አለበት። ይህ ሳይሆን ተገኝቶ የአስተዳደር በደል ደርሶብናል የሚሉ አካላት ሲመጡ፤ በመመሪያው ላይ የተቀመጠው ህግ ሳይፈፀም ሲቀር አስተዳደራዊ በደል ደርሷል ይባላል። በደል የደረሰበት አካልም በደል ተፈጸመብኝ ሲል አቤቱታውን ይዞ ይቀርባል። ተቋሙም አቤቱታውን መርምሮ የመፍትሄ ሀሳብ ይሰጣል።

የመፍትሄ ሀሳብን መስጠት ብቻ ሳይሆን ጉዳይን መርምሮ እስከመጨረሻ ድረስ ያስፈፅማል። በዚህም የበርካታ አቤቱታ አቅራቢዎች ጉዳይ ተፈፅሞላቸዋል። አሁን በምንመለከተው የስራ አካሄድ የተለያዩ መሻሻሎች ይታያሉ። ለአብነት ያህል 2014 በጀት አመት ላይ ከመጡት አቤቱታዎች ሰባ አምስት በመቶ ለሚሆኑት የመፍትሄ ሀሳብ ተሰጥቷል። ቀሪው ሀያ አምስት በመቶ ደግሞ በተለያዩ ምክኒያቶች ሳይፈጸሙ ቀርተዋል።

ይህም ሲባል አንደኛ ከተቋሙ የምርመራ ጥናት የሚነሳ ችግር አለ፤ ሁለተኛ መረጃ በቂ ባለማግኘት ሲሆን ሶስተኛው በተቋሙና በአቤት ባይ መካከል ስምምነት በሚደረስበት ጊዜ ጉዳዮች ላይፈፀሙ ይችላሉ።

የመፍትሄ የመስጠት አቅማችን ሰባ አምስት በመቶ ደርሷል ሲባል ትልቅ ስኬት ነው፤ ነገር ግን ህብረተሰቡ የሚያነሳው የመልካም አስተዳደር ችግር ስር የሰደደና ከሙስና በላቀ ደረጃ የሰፋና የከፋ በመሆኑ ስኬቱ እንደስኬት ላይታይ ችሏል። ሁሉንም የመልካም አስተዳደር ችግር ለመድረስም ከችግሩ ስፋት የተነሳም ከባድ እንዲሆን ሆኗል።

ከዚህም በላይ የአስተዳደር በደሎችን የሚያየው የእንባ ጠባቂ ተቋም ብቻ ሳይሆን የፍትህ አካላት፤ ፍርድ ቤቶች፤ የፀጥታ አካላትና የመንግስት ተቋማት የሚመለከቱት ሲሆን በእነዚህ ሁሉ ተከፋፍሎ የሚሰራው መልካም አስተዳደርን የማስፈን ስራ የተቋም ስራ ብቻ አለመሆኑን ህብረተሰቡ ሊረዳው ይገባል።

በአጠቃላይ ግን የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደር በደል ደርሶብናል ብለው ለቀረቡ አቤት ባዮች እንባቸውን የማበስ ተግባር ያከናውናል። ከዚህም በተጨማሪ ህገ መንግስቱ ተጥሶ ሲገኝ አስፈፃሚ አካላትን በሚያነቃ መልኩ የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ ጥቆማ ይሰጣል።

**አዲስ ዘመን፤ በተለያዩ ጊዜዎች በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለያዩ ጠንካራ መግለጫዎችን ታወጣላችሁ። ይህ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲቀረፉ ምን ያህል አስተዋፅኦ አድርጓል?**

**ዶክተር እንዳለ፤** መግለጫዎች የሚወጡት ወይም የሚተላለፉት ችግሮችን ለመቅረፍ ብቻ አይደለም። ችግሮችን ለመቅረፍ አንዱ መሳሪያ ሊሆን ይችላል። ከዛ ባለፈ ግን የመንግስት ውሳኔ ወይም ድርጊት ከህገ መንግስቱ እና ከህግ አንጻር ትክክል አለመሆኑን የተቋማችን አቋም ማሳወቅ ነው።

ያወጣችሁት ህግ፣ ያስተላለፋችሁት ውሳኔ ወይም አጠቃላይ አሰራሮች ከዜጎች ህገ መንግስታዊ መብት ጋር የሚቃረን ነው በሚል እናሳውቃለን።

ሌላው በዴሞክራሲ መርህ መሰረት በአንድ ጉዳይ መንግስት አቋሙን እንዲያሳውቅ ተጽእኖ ለማሳደር ነው መግለጫዎች የሚወጡት። ለምሳሌ መንግስት የህግ የበላይነትን በግልጸኝነት እና በተጠያቂነት መርህ እየሰራ አይደለም ብለን መግለጫ ብናወጣ፤ አይደለም መንግስት የህግ የበላይነትን እያስከበርኩ ነው፣ በግልጸኝነት እና በተጠያቂነት መርህ መሰረት እየሰራሁ ነው ይላል። ያንንም በተግባር ለማሳየት ይሰራል በመጨረሻ ህዝብ ፍርድ ይሰጣል ዲሞክራሲ የሚባለው ይህ ነው።

በአጠቃላይ መንግስት ትኩረት የሰጠባቸውን ጉዳዮች ማንሳት ይቻላል ለምሳሌ የብሄራዊ እና ደህንነት የተጠሪነት ጉዳይ፤ 12ኛ ክፍል ፈተና፤ የአዲስ አበባ ጉዳይ፤ መሰረታዊ ሸቀጥ አቅርቦቶችን ከአቅራቢዎች አንጻር የተለያዩ መግለጫዎች አውጥተን ብዙ የተፈቱ ጉዳዮች አሉ።

መግለጫ ከማውጣትም በላይ የተለያዩ ችግሮች የታዩባቸው አካባቢዎች ላይ ጥናት በማድረግ የችግሮቹን ስፋት እናሳያለን። ለምሳሌ በቅርቡ እየተተገበረ ያለው የነዳጅ ድጎማ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ነው አይደለም ? በሚል መነሻ የተለያዩ አካባቢዎች የትራንስፖርት ታሪፎችንና ሌሎች ማሳያዎችን በመመልከት ህብረተሰቡ በነዳጅ ድጎማው የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ እየሆነ አለመሆኑን በጥናቱ ተደርሶበታል።

> የፖለቲካ ገበያው መስፋት አለበት ሲባል ከገበያ የሚገዛው የመንግስት ወይም የብልጽግና ሃሳብ ብቻ አይደለም፡፡ የሁሉም ሃሳብ የብልጽግናን ጨምሮ ወደ ገበያ ይወጣል፤ ከዚያ ህዝብ ገዥው ሃሳብ ከገበያ ይሸምታል፡፡ ዴሞክራሲ የሚያድገውም በመሳሪያ ወይም በጡንቻ ሳይሆን በሃሳብ የበላይነት ነው

**አዲስ ዘመን፤ የሚዲያ ነፃነት እና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እስከምን ድረስ ነው?**

**ዶክተር እንዳለ፤** የመገናኛ ብዙኃን ነጻነት እና የሃሳብ ነጻነት መብት መሰረታዊ የዜጎች መብት ነው የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? ለምን ይህ መብት ሆኖ በህገ መንግስት እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች አካል ሊሆን ቻለ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ከዚህ አንፃር በየትኛውም ህገ መንግስት ከታየ የአንድ ሀገር ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት ህዝብ ነው ይላል። ይህን ካልን ህዝብ መብቱን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችለው እንዴት ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል።

የህዝቦች ሉዓላዊ መብት የሚገለፅበት አንደኛው መብት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ በሚያደርገው ምርጫ ነው። ሁለተኛው ህዝቡ በመንግስት ውሳኔዎች ፖሊሲዎች እና እቅዶች ላይ በቀጥታ መሳተፍ ሲችል ሲሆን ሶስተኛው መንግስት ለህዝቡ በገባው ቃል መፈጸሙን

# ተጠየቅ

ለመጠየቅ በአጠቃላይ መንግስት በተጠያቂነት እና በግልጸኝነት መርህ መሰረት መሰራቱን ማረጋገጥ መቻል አለበት።

የዜጎች መረጃ የማግኘት መብት እና የመገናኛ ብዙኃን መረጃን የማስተላለፍ መብት መከበር ያለበት ለዚህ ነው። የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነጻነት ህገ መንግስታዊ መብት ሊሆን የቻለው አንቀጽ 24/4 በግልፅ የተቀመጠ መብት ነው።

ከዚህ በመነሳት ከመገናኛ ብዙኃን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ፤ ለዜጎች መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶች ስለመከበራቸው እና በህዝቦች መካከል ነጻ ሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር የድርሻቸውን እንዲወጡ ለማድረግ የዜጎች ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በአዋጅም በህግም የተደነገገው ከዛ በመነሳት ነው።

ከዚህ አንጻር የሚዲያ ነጻነትን ማስከበርን በተመለከተ ወይም ህገ መንግስታዊ መርሆዎችን እስኪከበሩ፤ የሀገሪቷን ህጎች ባህሎች እሴቶች የዜጎችን ሰላምና ደህንነት እስካከበር ድረስ፤ መረጃን የመሰብሰብ የመቀበል እና የማስተላለፍ ህጋዊ ብቻ ሳይሆን ህገ መንግስታዊ መብት አላቸው።

ከኢትዮጵያ አንጻር የሚስተዋሉ ችግሮች አንዱ ከሚዲያዎች አደረጃጀት አንጻር ነው። በተለይ የመንግስት ሚዲያዎች ቦርድ አባላት የሚባሉት በፖለቲካ የሚሾሙ መሆናቸው ነጻና ገለልተኛ ሆነው እንዳይሰሩ ተጽእኖ ይኖርባቸዋል? ወይስ አይኖርባቸውም የሚለው ሀሳብም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው።

አንዳንድ መገናኛ ብዙኃን ክልላዊ አደረጃጀት በመሆናቸው የክልላቸውን ብሔር ባህል እሴቶች ማንነት እና ፍላጎት ማንጸባረቅ አለባቸው። ግን ደግሞ ፌደራላዊ ሀገር መሆናችንን ዘንግተው ከአንድነታችን ይልቅ በልዩነቶች ላይ ሲሰሩ ውለው ያድራሉ። ይህም በመሰረታዊነት ነፃነቱ በተገቢው መልኩ እንዳይተገበር ያደረገው ችግር ነው።

ከዚህም በተጨማሪ አስፈጻሚ አካላት በእጃቸው ያለውን መረጃ ያለ ስስት እየሰጡ አይደለም። አስፈፃሚ አካላት በእጃቸው ያለውን ማንኛውም መረጃ እንደተቋም ወይም እንደ ሀገር የዜጎችን ሰላምና ደህንነት የሚያውክ፤ የወጣቶችን ሰላምና ደህንነት የማይጎዳ እስከሆነ ድረስ፤ ወይም መረጃው ሚስጥራዊ ነው ተብሎ እስካልተለየ ድረስ በእጃቸው ያለ የመረጃ ሃብት የህዝብ ሀብት መሆኑን በማወቅ መስጠት ተገቢ ነበር። ነገር ግን አብዛኛው ተቋማት ይህንን ሲያደርጉ አይታዩም።

ሌላው የመረጃ ነፃነትን እንዲያስተገብሩ በአዋጅ ቁጥር 590/2000 የህዝብ ግንኙነት ሀላፊዎች የመረጃ ነፃነትን እንዲያስተገብሩ ስልጣን ተሰጥቷቸው እንደነበር ይታወሳል። አሁን ባለው ሁኔታ የትኛው የህዝብ ግንኙነት ነው የአንድ ተቋም ልዩ ምልክት ሆኖ የሚታየው ? ለምሳሌ ከዚህ ቀደም ተቋማት ሞዴል ወይም ምልክት የሚሆኑ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችና ሀላፊዎች ነበሩ።

ከህብረተሰብ እድገት አንጻርም በሰጠኸው ነጻነት ልክ መብትና ግዴታውን መሸከም ይችላል ወይ በማለት መጠየቅ ያስፈልጋል። ይህም ሲባል የሚዲያ ነፃነትን የሚሸከም ህብረተሰብ ሊኖር ይገባል። ህብረተሰብ ሚዲያን የሚያወቅ፣ አጠቃቀሙን የሚገነዘብ፣ የተላለፉ መረጃዎችን የሚመረምር ሊሆን ይገባል።

ጠቅላይ ሚንስትሩ ሰሞኑን የፖለቲካ ገበያው መስፋት አለበት የሚል ሀሳብ ሲያነሱ ነበር። ይህ የፖለቲካ ገበያው መስፋት አለበት ሲባል ከገበያ የሚገዛው የመንግስት ወይም የብልጽግና ሃሳብ ብቻ አይደለም። የሁሉም ሃሳብ የብልጽግናን ጨምሮ ወደ ገበያ ይወጣል ከዚያ ህዝብ ገዥውን ሃሳብ ከገበያ ይሸምታል። ዴሞክራሲ የሚያድገውም በመሳሪያ ወይም በጡንቻ ሳይሆን በሃሳብ የበላይነት ነው።

ለዚህ ደግሞ ሀሳብን በሀሳብ መሞገት መለመድ አለበት። መንግስት እንደ ግለሰብ ማሰብ የለበትም፤ ሆደ ሰፊ እና ታጋሽ መሆን አለበት።



ይህ ሲባል የዜጎችን መብት መደፍጠጥ መብቱ ነው ማለት አይደለም።

እኔ በግሌ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የምመኝላቸው እንደ ከ1801 እስከ 1809 የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እንደነበሩት ቶማስ ጀፈርሰን የአሜሪካ ዴሞክራሲ አባት እንደተባሉ ሁሉ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ አባት እንዲባሉ ነው። አባይ ግድብን ብንመለከት የቀድሞ ጠቅላይ ሚነስትር አቶ መለስ ዜናዊ ጀምረው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ለመጨረስ እየሰሩ ነው።

የፖለቲካ ገበያው ፍትሀዊ እና ነጻ እንዲሆን የሚዲያ ነጻነት መጠበቅ አለበት። ይህ ባልሆነበት የፖለቲካ ገበያው እንደ ሽቀጥ ደላሎች የሚመሩት ገበያ ይሆናል። በዚህ አጋጣሚ ጠቅላይ ሚንስትሩ ለማእከላዊ ኮሚቴ አባላት በማጠቃለያነት ያቀረቡትን ሃሳብ ወደ ፖሊሲ እቅድ እና ፕሮጀክት መለወጥ ካልቻሉ ሃሳባዊ ሆኖ ይቀራል።

**አዲስ ዘመን፤ ስመገናኛ ብዙኃን መረጃን ስሚከለክሉ ተቋማት የህዝብ እንባ ጠባቂ እስከምን ደረጃ ሄዶ ያስገድዳል ? መረጃ ያሰጣል ? ባይሰጡስ ሲያስጠይቅ የሚያስችል ህግ አለው ?**

**ዶክተር እንዳለ፤** መረጃ የሚከለክሉ ተቋማትን ተጠያቂ የሚያደርግ ህግ የለንም። በአዋጅ 590/2000 አንድ የመገናኛ ብዙኃን ተገቢ ያልሆነ ነገር አስተላልፎ ቢገኝ በገንዘብም በእስራትም የሚቀጣውን ቅጣት በግልፅ አስቀምጧል። በአንፃሩ ደግሞ አንድ አስፈፃሚ አካል መረጃ ባለመስጠቱ የተነሳ ተጠያቂ የሚያደርግ የህግ መሰረት የለም።

ነገር ግን ተቋሙ መረጃ መከልከልን እንደ አንድ አስተዳደራዊ በደል በመውሰድ በአዋጅ ቁጥር 1142 ተጠያቂ የሚደረግበት ሁኔታ አለ። ይህንን ያደረጉ አገልግሎት ሰጪዎችን በሚዲያ ከማጋላጥ አንስቶ ክስ እስከመመስረት ድረስ የሚደርስ ሁኔታ አለ።

እዚህ ጋ ግን አንድ ሚዲያ አንድን መረጃ የሚፈልገው ለዜና ወይንም የሆነ ወቅቱን ለጠበቀ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ህጉ የሚያስቀምጠው አንድን የመንግስት አስፈፃሚ አካል መረጃ አልሰጠህም ብሎ ለመክሰስ ከ90 ቀን እስከ 120 ቀን መጠበቅ ያስፈልጋል። ይህም መገናኛ ብዙኃን ወደ ተቋሙ እንዳይመጡ ወይም ክስ እንዳይመሰርቱ አንዱ እክል ነው። ይህንንም ችግር ለመቅረፍ አዲሱ አዋጅ ይረዳል ብዬ አስባለሁ።

አዲስ የመረጃ ነፃነትን ሊያስጠብቅ ይችላል ተብሎ የታመነበት አዋጅ ተረቆ ወደ ስራ እየገባ ነው። ይህም መረጃ አልሰጥም ያሉትን ለመክሰስ፤ ከ90 እስከ 120 ቀናት መጠበቅ አለበት የተባለውን ቀን የሚቀንስ እንዲሆን እየተሰራ ነው። አዋጁ ላይ እንደተቀመጠ በ10 ቀን ውስጥ መስጠት አለበት ካልሆነ ግን ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ አለ።

**አዲስ ዘመን፤ መረጃ አልሰጥ አሉን ብሎ የከሰሰ ጋዜጠኛ ወይም ተቋም እንዲሁም ስጋዜጠኞች አልሰጠህም ተብሎ የተጠየቀ ተቋም ካለ ቢገልፁልን?**

**ዶክተር እንዳለ፤** ዘንድሮ አንድም የሚዲያ ተቋምም ሆነ ጋዜጠኛ ወደ ተቋሙ መረጃ ተከለከልኩ ሲል አቤቱታ አላቀረበም። ከዚህ ቀደም ግን ፕሬስ ድርጅት፤ ኢሳትና፤ ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አቤቱታቸውን አቅርበው ነበር።

እንደምሳሌ ባነሳለሽ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኛ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ህዝብ ግንኙነት ጋር ደውሎ መረጃ ባለማግኘቱ የተነሳ ያቀረበው አቤቱታ ነበር። ይህን አቤቱታ ይዘን ዋና ስራ አስፈፃሚው ጋር ባደርግነው ግንኙነት የተነሳ ችግሩ እንዲፈታ ሆኗል።

የወንጀል ነክ ጉዳዮች ሆነው ጉዳዩ ፍርድ ቤት እያለ ፖሊስ ጋር መረጃ ተጠይቆ መረጃውን ማግኘት አልቻልኩም የሚል ክስ ወደተቋሙ ሲመጣ ያለውን ሁኔታ አጣርቶ ትክክለኛ የመረጃ ምንጭ ወደሆነው ተቋም ጥቆማ ተሰጥቷል። ከተቋማት ጋር በሚኖር ግንኙነት የሚፈቱ ችግሮች አሉ፤ ሪፎርም ውስጥ ቆይተው ሪፎርሙ ሲጠናቀቅ መረጃ እንዲሰጣቸው የተደረገበትና ሌሎችም አሉ።

**አዲስ ዘመን፤ ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ ሀሳብ የሚያስተላልፉ፤ የሌሎችን ሰብዓዊ መብት የሚጥሱ በምን ይጠየቃሉ? አንዳንዶች ማህበረሰቡን የሚጎዳ ንግግር እየተናገሩ ህጋዊ እርምጃ ሲወሰድባቸው የመናገር ነፃነታችን ተነፈግን ሲሉ ይደመጣሉ። ይሄ በምን አግባብ ይታያል ?**

**ዶክተር እንዳለ፤** ይህንን ጉዳይ የሚያነሳው መንግስት ወይንስ ህዝብ ነው የሚለው ጉዳይ ተለይቶ መቀመጥ ይኖርበታል። አንድ የመንግስት ተቋም እገሌ የሚባል ሚዲያ አለአግባብ ስሜን አጥፍቷል ብሎ ቢጠይቅ ያንን ያስተላለፈው ሚዲያ መረጃውን እንዲያስተባብል ይደረጋል።

ከዛ ባለፈ ወደ ክስ ወይም ጋዜጠኞችን ወደ ማሰር ከተሄደ ኢ- ህገ መንግስታዊ ነው። ተገቢ አይደለም። የወጣቶችን ደህንነት የሚነካ፤ መልካም አስተዳደር ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር፤ የሀገር ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥል፤ የግለሰቦችን ክብር በሚነካ መልኩ የማንቋሸሽ ስራ የሚሰሩ የመገናኛ ብዙኃን ካሉ ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር አዋጅ ቁጥር 11/85ና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ የሚታይ ይሆናል።

መገናኛ ብዙኃን እነዚህን ተግባር ፈፅመው ሲገኙ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን የመቆጣጠርና በአዋጁ መሰረት ተጠያቂ የማድረግ ስራን ይሰራል። አብዛኛው ማህበራዊ መገናኛ ብዙኃንን መቆጣጠር የማይቻልበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህንን ችግር ለማስቀረት ህብረተሰቡ ማህበራዊ ሚዲያዎችን ለልማት፣ ለሰላም፣ ህብረተሰብን ከህብረተሰብ ጋር ለሚያቀራርብ ነገሮች እንዲያውሉ ግንዛቤ መስጠትም የተሻለ መፍትሄ ነው። አንድ ሰው ሊቀጣ ወይም ሊታሰር መቻሉ ግን ዘላቂ መፍትሄን ለማምጣት ባለመቻሉ የህብረተሰቡን ንቃተ ህሊናን መጨመር ያስፈልጋል።

ሀሳብን በሙዚቃ ወይም በግጥም ወይም በሌላ አይነት የመግለጽ የዜጎች መብት ግን ሃሳቡ ትክክል አይደለም የሚል ወገን ትክክል አለመሆኑን በሃሳብ ነው መግለጽ የሚችለው እንጂ መክሰስ አይችልም።

ለምሳሌ ያህል ከሰሞኑ አንድ ጋዜጠኛ ከቆላ ስንዴ እና ከፕሮጀክቶች ጋር ተያይዞ ያነሳው ሃሳብ ፖሊቲሳይዝድ ተደርጎ በየማህበራዊ ሚዲያ ሲዘዋወር አይተናል። ጋዜጠኛው ለስንዴ የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ለምን ለድንች ወይም ለሌሎች የግብርና ውጤቶች አልተሰጠም በማለት ይህንን መመርመር እፈለጋለሁ ሲል ይህንን ለመመርመር የፈለከው ምን አስበህ ነው ? በሚል መረጃን መከልከል ተገቢ አይደለም።

የአንድ ጋዜጠኛ ሃሳብ አልፋና ኦሜጋ ነው ያለው ማነው? በምርምራ ጋዜጠኝነት ልመርምር ቢል ከጀርባ የፈለገ ተልእኮ ይኑረው ከጋዜጠኛው የሚጠበቀው ተአማኒና ሚዛኑን የጠበቀ ዘገባ እንዲሆን ማድረግ ነው ።

**አዲስ ዘመን፤ ተቋሙ በቅርቡ የተለያዩ ጠንካራ ሀሳቦች ያላቸውን መግለጫዎች ሲያወጣ ቆይቷል። አሁን ምን ስለተገኘ ነው ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ ወደፊት መምጣት የተጀመረው የሚሉ አስተያየቶች እየተነሱ ነው። በዚህ ላይ ምን ምላሽ አለዎት?**

**ዶክተር እንዳለ፤** ምንም የተለየ ነገር ስለተገኘ አይደለም። በጦርነቱ ወቅት እንደ አንድ ለሀገሪቱ ሰላም እንደሚጨነቅ አካል ዝምታን መርጠናል። በተቀረ ግን ከዚህ በፊትም ከዚህ የጠነከሩ መግለጫዎች አውጥተናል።

በቅርብ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ፈተና ላይ የሰጠነው መግለጫ ነበር፤ በአንድ ወቅት በኦሮሚያ እና በቤንሻንጉል ለደረሰው የዜጎች ሞትና መፈናቀል ከመንግስት የጸጥታ ሀይሎች በላይ ሳይሆን በመንግስት ቸልተኝነት የተፈጠረ መሆኑን አንስተን ሞግተናል።

የአሁኑ የገነነው ምናልባትም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ትኩረት የሚሰጥበት ጉዳይ በመሆኑ አዲስ ነገር ሊያስመስለው ችሎ ይሆናል። ህገ መንግስት በመሰረቱ መንግስት ህዝብን የሚቆጣጠርበት ሳይሆን ህዝብ ለመንግስት በህገ መንግስቱ መሰረት አስተዳድረኝ ይህንን ከላደረግክ በህገ መንግስቱ እጠይቅሃለሁ በማለት ህዝብ መንግስትን የሚቆጣጠርበት ነው።

ስለዚህ ህገ መንግስቱ በተገቢው መልኩ አገልግሎት ላይ ካልዋለ፤ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ስራቸውን እየሰሩ ነው፤ እየሰሩ አይደለም የሚለውን ይጠይቃል። ህገ መንግስቱ ሊሻሻል ይችላል። ህገ መንግስቱን እስካላሻሻላችሁ ድረስ በህጉና በህገ መንግስቱ መሰረት መስራት አለበት በማለት መንግስትን እየሞገትን ነው ያለነው።

ዋናው ነገር መንግስት ከለውጡ በኋላ የዴሞክራሲ ተቋማት ነጻ እና ገለልተኛ ግን ደግሞ በህግ መሰረት እንዲሰሩ ነጻነት ሰጥቷቸዋል። በመሰረቱ ይህን መብት ሊሰጥም ሊነፍግም መብት የለውም። ግን የዴሞክራሲ ተለማማጆች በመሆናችን መንግስት ሁኔታዎችን እንዳመቻቸ እንቆጥረዋለን። ይህን እድል ያለመጠቀም የመሪዎች ድክመት ነው ፤ ተቋም መገንባት አለመቻል የተቋማቱ ድክመት ነው።

በአጠቃላይ ህብረተሰቡ ሌላ መብቱን የሚያስጠብቅለት አካል ከመጠበቅ ይልቅ በየደረጃው ያለውን የመልካም አስተዳደር ችግር በመቃወም፤ በእጅ መንሻና በሌሎች ጉዳዮች ጉዳይን ከመፈፀም ይልቅ በመብቱ መገልገልን ቢለማመድ ሀገሪቱ እውነተኛ ዲሞክራሲ ይሰፍንባታል ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፤ ውድ ጊዜዎን ሰውተው ስቃስ ምልልሱ ፈቃደኛ ስስሆኑ በአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ስም ከልቤ አመሰግናስሁ።**

**ዶክተር እንዳለ፤** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## የሰላምን መንገድ በሰላማዊ ተግባቦት እናጽና

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

ሰላም ቀዳሚ መገኛዋ ቀና ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ሰላማዊ ተግባቦት ነው። ከሰላማዊ ተግባቦት ውጪ የተሟላ ሰላምን ሊያመጣ የሚችል ነገር ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆንም አይቻልም። ምክንያቱም ሰላማዊ ተግባቦት ሰላምን ማዕከል በማድረግ አገርና ህዝብን አስቀድሞ ፖለቲካዊ መሻትን ያስከተለ ነው። ሰላማዊ ተግባቦት ሁሉም ሰው የተለየ እና ልዩ ልዩ ሀሳብና ፍላጎት እንዳለው በመረዳት ያን ብዙ አይነት ሃሳብ ወደ ጠቃሚ አንድ ሀሳብ መቀየር ነው። ሰላማዊ ተግባቦት የራስን ፍላጎት ወደጎን ብሎ የብዙሀኑን ፍላጎት ማስቀደም ነው። ይሄ ሁሉ ባልሆነበት ሁኔታ ላይ ሰላም ሊመጣ አይችልም። ሆኖም በዘመናት ሂደት ውስጥ ለሚያጋጥሙን ሰላምን የሚያደፈርሱ ሁነቶች የሰላም መገኛዎችን ዘግቶ የመኳዛችን ውጤቶች ናቸው።

ምክንያቱም የሰላም መንገድን ዘግቶ፣ ቀና እሳቤዎችን አርቆ፣ ከሰላማዊ ተግባቦት ተነጥሎ ሰላም ለማምጣት መሞከር አይቻልም። ይሁን እንጂ ሰላም ሊሰጡንና ሊያግባቡን የሚችሉ ብዙ የጋራ ትውፊቶቻችንን ችላ ብለን በሚለያዩን ጥቂት ነገሮች ላይ ጊዜ ስናጠፋ ከርመናል። ይሄ አካሄድ ደግሞ የምንፈልጋትን አገር አልፈጠረልንም። በመሆኑም የምንፈልጋትን አገር እውን ለማድረግ በምናደርገው ጉዞ ይሄን የኖረ አቅጣጫችንን መቀየር፤ ባልሄድንባቸው መንገዶች መሄድ፣ ባልተመለከትነው አቅጣጫ መመልከት ይኖርብናል።

ብዙዎች የሰላምን መገኛ መንገድ ሳያውቁ ሰላም ለማምጣት ብዙ ለፍተዋል። ሆኖም ሰላም አንድ ቦታ ነው ያለው፤ እርሱን በመነጋገር ውስጥ ነው። መነጋገር ስንል መግባባት ያለበትን መነጋገር ነው። ዓለም ሁሌም በመነጋገር ውስጥ ናት፤ ሁሉም መነጋገሮች ግን ሰላም ሲያመጡላት አይታይም። ይሄ የሆነው ደግሞ በራስ ወዳድነትና የአንድ ወገንን የበላይነት በማሳየት ነው። የአንድ ወገን የበላይነት በሚንጸባረቅበት ሁኔታ ላይ ሰላም የለም። ሰላም የእኩል ሀሳብ፣ የእኩል ተግባር ነጸብራቅ ነው። አገራችን ለምን ሰላም ራቃት ብለን ስንጠይቅ ይሄን እውነት ነው የምናገኘው። እኛ አገር ሁሉም ነገር በእኩልነት ላይ ሲንፀባረቅ አይታይም። ፖለቲካችንን ብናየው የእኔነት እና የራስ ወዳድነት እድፍ ያቆሸሸው ነው። ይሄ ግለኝነት ደግሞ መጨረሻው ጦርነት ነው። እንደ አገር ዘላቂ ሰላም ለመገንባት ይሄንን መንገድ መቀየር ይኖርብናል።

አንድ አይነት ታሪክ አገር አይገነባም፤ ትውልድ አያሻግርም። ከኖርበት የጦርነት ልማድ ወጥተን መነጋገርን መሰረት ያደረገ አዲስ አብዮት ያስፈልገናል። ከነበርንበት የቂመኝነት አካሄድ ወጥተን እርቅን ያስቀደመ አዲስ የይቅርታ አስተሳሰብ መላበስ ያስፈልገናል። አገራችን አሁን የሰላም አብዮት ነው የሚያስፈልጋት። የአንድነት፣ የመቻቻል አብዮት ነው የሚያስፈልጋት። ይሄን አዲስና ለዘመኑ የሚመጥን አካሄድ ነው መለማመድ ያለብን። ለመነጋገር ከተሰናዳን ከጦርነት የሚሻሉ ብዙ ነገሮች አሉን። ቀድማ የነበረችው አገራችን ዛሬ ላይ በብዙ ነገር ላይ ወደኋላ ቀርታለች። በዚህ ላይ ጦርነትና አለመግባባት ሲጨመርበት ደግሞ ችግሩን ያገዝፈዋል።

በየትኛውም መስፈርት እንየው ለአገራችን ጦርነት ሳይሆን ሰላም ነው የሚያስፈልጋት። ለህዝባችን መለያየት ሳይሆን አንድነት ነው የሚያስፈልገው። የተጀመረው ሰላም እንዲቀጥል፣ ቀጥሎም አስተማማኝ እንዲሆን ከትላንቱ የተለየ አዲስ ማንነት ያስፈልገናል። በዚህ አዲስ አስተሳሰብ፣ አዲስ ፖለቲካ፣ አዲስ ርዕዮተ ዓለም ካልሆነ አዲስና ሰላማዊ አገር መፍጠር አይቻለንም። እውነተኛ ሰላም ተነጋግሮ በመግባባት ውስጥ ነው የሚገኘው። ሰው ተነጋግሮ መግባባት ካልቻለ አገር ሊለውጥ የሚችል እውቀትም ሞራልም እንደሌለው ነው የማምነው። ጥበብ ማለት.. እውቀት ማለት በብዙሀነት ውስጥ አንድ አገርና አንድ ህዝብ መፍጠር ነው። ምርጥ ፖለቲከኛ ምርጥ ተናጋሪ ሳይሆን ምርጥ አሳቢ ነው። ምርጥ ሀሳቦቻችን ናቸው ምርጥ አገር የሚፈጥሩልን። ምርጥ ሃሳቦቻችን ናቸው በብዙ ተቃርኖ፣ በብዙ የፖለቲካ ልዩነት ውስጥ ለአገር የሚበጅ እውነት የሚሰጡን። ምርጥ ሀሳቦቻችን ናቸው ከኋላቀርነትና ከአዝጋሚ ጉዞ የሚያወጡን። ተነጋግሮ መግባባት ያልቻልነው ለአገር የሚበጅ፣ አገርን ያስቀደመ፣ ከእኔነት የወጣ ምርጥ ሀሳብ ስለሌለን ነው።

ምርጥ ሀሳብ ሁልጊዜም ማረፊያው አገርና ህዝብ ነው። በቀሪ ጊዜያችን በምርጥ ሀሳብ ምርጥ አገር መፍጠር አለብን። በምርጥ ሀሳብ ምርጥ አገር ካልፈጠርን በብላሽ ሀሳብ ብላሽ አገር ፈጥረን ተበላሽተን ነው የምንቀረው። ይሄ ደግሞ ለማናችንም አይበጅም፤ በእርቅና በቀና ተግባቦት ወደ ሰላም መሄዱ ነው ለሁላችንም እኩል ዋጋ ያለው።

አገራችን ሀሳብ አላጣችም፤ እንደ ህዝብ ቁጥሯ፣ እንደ ወጣቷ ብዛቷ ለአገር የሚሆን ብዙ ሀሳብ አለን። ችግር የሆነብን የሀሳብ ልዩነቶቻችንን ወደአንድነት ማምጣቱ ላይ ነው። ችግር የሆነብን ልዩ ልዩ ሀሳቦቻችንን እንዴት በሰላማዊ መንገድ ለሰላማዊ ነገር መጠቀም እንዳለብን አለማወቃችን ነው። በአግባቡ መጠቀም ከቻልን የተለያዩ ሀሳቦች በአንድ አገር ላይ ልማትም፣ ብልጽግናም ናቸው። በአግባቡ መጠቀም ካልቻልን ደግሞ ነውጥና ጦርነትን ነው የሚያስከትሉብን። አሁን የሚጠቅመን የሀሳብ ብዙሀነታችንን በሰላማዊ መንገድ ለልማት መጠቀም ነው። ያለፉ የጦርነት ታሪኮቻችን የሀሳብ ብዙሀነትን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ካለማወቅ የመጣ ነው። አንድ ሰው አንድ ሀሳብ ሲኖረው፣ አንድ ፖለቲከኛ ከሌላው ፖለቲከኛ አዲስ ሀሳብ ሲኖረው በራሳቸው መንገድ ሁሉም ለኢትዮጵያ አስተዋጽኦ እያደረጉ እንደሆነ ማወቅ አለብን። የትኛውም የሀሳብ ልዩነት ወደጦርነት ከማምራቱ በፊት ጠቃሚ ነው።

የሀሳብ ልዩነቶቻችን ኢትዮጵያን እንዲጠቅሙ እንጂ እንዲጎዱ መፍቀድ የለብንም። የፖለቲካ ልዩነታችን አገር እንዲቀይሩ ህዝብ እንዲያሻግሩ እንጂ ለጦርነትና ለጉስቁልና እንዲዳርጉን መፍቀድ የለብንም። እኛ አገር ፖለቲካውም ሆነ ፖለቲከኞቻችን ኢቲክሱ ከሚፈቅደው ውጪ ነው እየፈነጩ ያሉት። ይሄ ብላሽ አካሄድ ነው የሀሳብ ልዩነትን በአግባቡ እንዳንጠቀም እክል እየፈጠረብን ያለው። አገርና ህዝብን ያስቀደመ ፖለቲካና ፖለቲከኛ በሀሳብ ልዩነት አገር ይሰራል እንጂ ጦርነት አይፈጥርም። ከእኛ በፊት ኢትዮጵያ መቅደም አለባት። ከእኛ በፊት ህዝብ መቅደም አለበት። ከስልጣናችን በፊት፣ ከግል ጉዳያችን በፊት ትውልድ ይቅደም። ከአገር በፊት የግል ጉዳያችንን ማስቀደማችን ነው ዛሬ ላይ ለጦርነት እያዳረገን ያለው። ኢትዮጵያን እስካላስቀደምን ድረስ የምንፈልገውን ሰላም ማምጣት አንችልም። ኢትዮጵያን እስካላስቀደምን ድረስ አሁንም ቢሆን ተነጋግሮ ሰላም ማምጣት ይቸግረናል።

> **በየትኛውም መስፈርት እንየው ለአገራችን ጦርነት ሳይሆን ሰላም ነው የሚያስፈልጋት። ለህዝባችን መለያየት ሳይሆን አንድነት ነው የሚያስፈልገው። የተጀመረው ሰላም እንዲቀጥል፣ ቀጥሎም አስተማማኝ እንዲሆን ከትላንቱ የተለየ አዲስ ማንነት ያስፈልገናል**

አገር በአንድ አይነት ሀሳብ አትገነባም። ለአገር ግንባታ አሁን ላይ እዚም እዛም የሚሰማ ልዩ ልዩ ሀሳብ ያስፈልገናል። ልዩ ልዩ ሀሳቦቻችን ብልህነትን፣ ስኬትን፣ ተስፋን፣ እውቀትን፣ ልምድን ያነገቡ ናቸው። በሰላማዊ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ የሃሳብ ማዕድ ዘርግተን እንወያይባቸው። ከዚህ በዘለለ የአንተ ሀሳብ ከእኔ ሃሳብ አይገጥምም ብለን ወደመለያየት መግባት አይኖርብንም። ኢትዮጵያ መልከ ብዙ ናት ማለታችንም ለዚህ ነው። የተለያዩ መልኮች፣ የተለያዩ ባህሎች፣ የተለያዩ ወግና ስርዐቶች ያቆነጇት፤ በብዝሃነት የቆነጀ ማንነቷም ለከፍታዋ አቅም የሚሆናት ነው።

ታዲያ ይሄን አቅም የሚሆን የብዝሃነት ውበት ገፍቶና ማስተናገድ ሳይቻል ቀርቶ ይቺ አገር እንዴት ሆና በአንድ አይነት ሀሳብ ብቻ ትቀጥላለች? ምክንያቱም ኢትዮጵያ ብዙ ናት፤ ብዙ ሀሳብ፣ ብዙ እይታ ያስፈልጋታል። የሀሳብ ልዩነቶቻችን ወደጦርነት እንዳይወስዱን ተነጋግሮ መግባባትን መልመድ አለብን። ተቻችሎ በጋራ መቆምን ባህል ማድረግ አለብን። የመጣው ሰላም በሁላችንም ልብ ላይ ተስፋን ለኩሷል። ሳቅ አድርጎልናል። እንደሳቅን እንድንቀጥል ሰላማችን እክል ሳይገጥመው መዝለቅ አለበት። ይሄ እንዲሆን ደግሞ ሰላም በሚያመጡ ነገሮች ላይ ብቻ እናተኩር።

ጦርነት በቃን፤ ይሄ የሁሉም ኢትዮጵያውያን የጋራ ድምጽ ነው። በወንድማማች መካከል ፍቅር እንጂ መለያየት ዋጋ የለውም። ሲገሉንና ስንገልባቸው የነበሩ ሾተሎቻችን ወደ ሰገባቸው ይመለሱ። ሲያደሙንና ሲያጎሳቁሉን የነበሩ ጎራዴዎቻችን ወደ አፎታቸው ይመለሱ። ፍቅር ነው የሚያስፈልገን፤ ወንድማማችነት ነው የቀረን። ብዙ ነገሮችን ሞክረናል..አሁን የሚቀረን ሰላምና እርቅ ነው። አሁን የሚቀረን ተነጋግሮ መግባባት፣ ተግባብቶ ሰላማዊ አገር መፍጠር ነው። ጦርነት የፈጠሩ ሀሳቦቻችንን ሰላም እንዲፈጥሩ እናድርጋቸው። መለያየትን የፈጠሩ ሀሳቦቻችንን አንድነትና ወንድማማችነትን እንዲያጸኑ እናስገድዳቸው።

ኢትዮጵያ ቤታችንም፣ የማር ቀፏችን ናት፤ ማር እንድትይዝ አርቀን የሰቀልናት ቀፏችን። ግን ማር አበባ በሌለበት ምንድነው? ማር ንብ በሌለበት ምንድ ነው? አገራችን ማር እንድትይዝ ማር ሊሰጧት የሚችሉ ነገሮች ያስፈልጓታል። ከዚህ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሰላም ነው። አበባ በሌለበት ማር እንደሌለ ሁሉ ሰላም በሌለበትም አገር ምንም ናት። አገራችን ማር እንድትይዝ፣ ህዝባችን ከማሩ እንዲበላ ማር የሚሰራ ሰላም ያስፈልገናል። ይሄ ባልሆነበት ሁኔታ ላይ ድካማችን ከንቱ ድካም ነው የሚሆነው። አንድን ነገር ስንፈልግ ያ ነገር የሚያስፈልገውን ግብዐት አሟልተን ነው መሆን ያለበት። አሁን ላይ አገራችን ከሰላም ውጪ ምንም አያስፈልጋትም። የአገራችን ሰላም ደግሞ ከሰማይ የሚወርድ ሳይሆን በእኛ በልጆቿ የሚፈጠር ነው። በመግባባት፣ በውይይት የሚመጣ ነው። ፖለቲካውን በማስተካከል፣ የሀሳብ ልዩነቶችን ወደተግባቦት በመቀየር የሚመጣ ነው።

ዓለም እንደ ሰላም የክብር አክሊል የላትም። ሁሌም ጸጋዎች፣ ሁሉም ክብሮች ከሰላም ቀጥለው የሚመጡ ናቸው። ብዙ ነገር እያለን ምንም እንደሌለው የሆንነው ከሁሉም ትልቁ ሰላም ስለጎደለን ነው። ይሄን ጉድለት በሰላም ካልሆነ በምንም አንሞላም። በሰላም መንገድ ከተጓዝን ብቻ ነው የኢትዮጵያን ችግሮች መፍታት የምንችለው። በምክክር መኖር ስንችል ብቻ ነው ለኢትዮጵያ የምንበጀው። እንደ አገር በሰላማዊ ሃሳብ የቆመች ሰላማዊ አገር ታስፈልገናለች። እናም ሁላችንም የሰላም ድልድይ እንሁን፤ ማንም ወጥቶ የሚገባበት ድልድይ። በሰላም ሀሳብ የተገነባ ድልድይ። ከዚህ ወደእዛ መሻገሪያ ድልድይ ያስፈልገናል። የጥል ግድግዳዎችን አፍርሰን፣ የመለያየት ግንቦችን ደርምሰን አዲስ ምስራቅ ማየት አለብን። አዲስ ፀሐይ፣ አዲስ ጀምበር መሞቅ አለብን። ለዚህም ወደ ጦርነት የሚወስዱ መንገዶችን እየዘጋን የእርቅና የምክክር መንገዶችን መክፈት አለብን። የመለያየት መንገዶችን እየዘጋን የአንድነትና የወንድማማች መንገዶችን መስራት አለብን። የተስፋዋ ኢትዮጵያ በዚህ እውነት ውስጥ ብቻ ነው የምትፈጠረው።

አገር ሰው ከሌለባት ምንም ናት። ሰው አገር ከሌለው ምንም ነው። አገርና ሰው፣ ሰውና አገር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። ሰው በአገር..አገር በሰው ነው የሚከበሩት። አገር በሰላም ካልሆነ በምንም አትቆምም። ሰው በሰላም ካልሆነ በምንም አያምርም። ሰላም ስናጣ፣ አንድነት ሲርቀን የአገራችንን መሰረት እየነቀነቅን ነው። ተነጋግሮ መግባባት ሲያቅተን፣ ተቻችሎ መኖር ሲከዳን የአገራችንን መሰረት እየገፋን ነው። በእኛ ሰላም ማጣት ከእኛ ውጪ የሚጎዳ ማንም የለም። ሰላም ባጣንባቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ ሁሉንም አይነት መከራ አይተናል። አሁን ስለሰላም የምንጮህበት ጊዜ ነው፤ አሁን የመጣው ሰላም እንዲቀጥል የምንታገልበት ጊዜ ነው።

ኢትዮጵያን እንስራ። ግዙፍም ብዙም ሆና ያነሰችውን፣ እልፍ ሆና የጎደለችውን አገራችንን እንታደግ። ሰው ሳታጣ ሰው ያጣችውን፣ ሀሳብ ሳታጣ ሀሳብ ያጣችውን አገራችንን እንማግር። ታሪክ ሞልቷት ታሪክ ያጣችውን አገራችንን እናድስ። በሰላሙ ዋዜማ ጥላቻ የሞላቸው አሮጌ አቆማዳዎቻችን በአዲስ መተካት አለባቸው። የፖለቲካ እድፍ ያቆሸሻቸው ትርክቶች በምክንያታዊ አሳቦች መሞላት አለባቸው።

ከእንግዲህ ጭንቅላቶቻችን የመፍትሄ ሀሳብ እንጂ የጦርነት ሀሳብ ማምጣቸው ይበቃል። ከእንግዲህ ልቦቻችን የይቅርታና የፍቅር ቦታ እንጂ የመለያየት ቦታ መሆናቸው ያበቃል። ከእንግዲህ ጀርባዎቻችን በጥላቻ መጉበጥ የለባቸውም። ከእንግዲህ ፖለቲከኞቻችን የእርቅ ሀሳብ እንጂ በመለያየት ሀሳብ ጊዜ ማጥፋት የለባቸውም። ከእንግዲህ በሚያግባቡንና በሚያስተቃቅፉን የጋራ ጉዳዮቻችን ላይ እንምከር። ከእንግዲህ ኢትዮጵያን ከፍ በሚያደርጉ ተግባራት ላይ እንሳተፍ። በሰላማዊ ተግባቦት እጦት ዝቅ ያለችውን አገራችንን ከፍ ማድረግ ይጠበቅብናል። በአገራዊ ምክክር አዲስና ነባር ችግሮቻችንን እየቀረፍን ሰንኮፏን የጣለች ኢትዮጵያን እንውለድ። ለዛሬው አበቃሁ፤ ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## በቤት ሥራ የታጀበው የውጭ ንግድ ገቢ አበረታች ጉዞ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የውጭ ንግድ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ነው። የኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው የውጭ ምንዛሬ ገቢን በማሳደግ የአገር ኢኮኖሚ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችለው ሥራዎች በመሥራት የውጭ ንግድን /የኤክስፖርት/ በማስፋት በከፍተኛ ደረጃ የማሻሻል ሥራ መሥራት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ኢኮኖሚው በሚፈልገው መጠን ተንቀሳቅሶ ከውጪ ምንዛሬ የሚገኘውን ገቢን ለማሳደግ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ጥራትን ማዕከል ያደረገ መጠን፣ አይነትና ስብጥር መጨመር እንዲሁም የውጭ ንግድ ስትራቴጂን በማስፋት በይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራበት እንደሚገባ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ።

የውጭ ንግድ መስፋፋት ከፍተኛ ደረጃ መድረስ የተነቃቃ እና ሳቢ የዓለም ገበያ ፍላጎት መኖር ወሳኝ ነው። ከዚህ ባሻገር ምርቶችን በክምችት የመያዝ አዝማሚያዎችን በመግታት፣ የሕገወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥሩን በማጠናከር፣ የድንበር ላይ ንግድ አፈጻጸሙን ከሕጋዊ አሠራሩ ጋር የማስተሳሰርና የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት እንደሚያስፈልግም መረጃዎች ያመላክታሉ።

በአገራችን ባለፈው በጀት ዓመት የወጪ ንግድ ለማሻሻል የተሰራው ሥራ ለውጥ ያስገኘና የተሻለ ውጤት የተመዘገበበት እንደሆነ ተመላክቷል። በ2015 በጀት ዓመት ከወጪ ንግድ 5 ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት የታቀደ ሲሆን፤ ይሕም በ2014 ከተገኘው ገቢ በ30 በመቶ ለማሳደግ የሚያስችል እንደሆነ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ክትትል ከሚያደርግባቸው ዘርፎች ደግሞ ባለፈው 2014 በጀት ዓመት ከተገኘው 906 ነጥብ 27 ሚሊዮን ዶላር በ28 ነጥብ 19 በመቶ በማሳደግ 1ነጥብ 16 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት መታቀዱንም ነው መረጃው የሚያመላክተው። ለምሳሌ፣ በዘንድሮ በጀት ዓመት 221 ሺ 916 ቶን የቅባት እህሎች በመላክ በ2014 ከዘርፉ ከተገኘው 263 ነጥብ 78 ሚሊዮን ዶላር ገቢ በ26 ነጥብ 2 በመቶ በማሳደግ 333 ነጥብ 02 ሚሊዮን ዶላር፤ እንዲሁም 274 ሺ 785 ቶን የጥራጥሬ ምርቶችን በመላክ ባለፈው በጀት ዓመት ከዘርፉ ከተገኘው 213 ነጥብ 306 ሚሊዮን ዶላር ገቢ በ22ነጥብ3 በመቶ በማሳደግ 262 ነጥብ 176 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት መታቀዱን ነው የሚኒስቴሩ መረጃ የሚያመላክተው።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከውጭ ንግድ ሊያገኘው ያቀደውን የውጭ ምንዛሬ በዚህ መልኩ የሚገለጽ ሲሆን፤ ይሄን ከማሳካት አኳያም ባለፉት አምስት ወራት በርካታ ስራዎች መከናወናቸው ተነግሯል። በዚህም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ በአምስት ወራት ውስጥ ለመፈጸም ካቀደው 1ነጥብ 528 ቢሊዮን ዶላር ማግኘቱን ነው የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አቶ መስፍን አበበ የሚኒስትሩ አማካሪ የገለጹት።

በውጭ ንግድ በአምስት ወራት ውስጥ ለማግኘት ከታቀደው 1 ነጥብ 8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ውስጥ 1ነጥብ 528 ቢሊዮን ዶላር ማግኘት መቻሉን የገለጹት አቶ መስፍን፤ ይህም የእቅዱን 80 ነጥብ 4 በመቶ ያህል እንደተፈጸመ የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመዋል። በውጭ ንግድ በአምስት ወር ውስጥ የተመዘገበው ውጤት ከዓምና ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የዘንድሮ በጀት ዓመት የአምስት ወራት አፈጻጸም ቅናሽ ማሳየቱን ጠቅሰው፤ የ2014 አፈጻጸም 1ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር እንደነበር አስታውሰዋል። አጠቃላይ የአምስት ወሩ የውጭ ንግድ ገቢ 87 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ እንዳለው ነው አቶ መስፍን የሚገልጹት።

በዘርፉ ስንመለከት ግብርና 85 በመቶ፣ ማኑፋክቸሪንግ 72 በመቶ፣ ማዕድን 36 በመቶ እና ሌሎች ምርቶች 138 በመቶ አፈጻጸም አሳይተዋል። ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር በዘርፍ ሲነጻጸር ግብርና 63 ሚሊዮን ዶላር ጨምሯል፤ ማኑፍክቸሪንግ 20 ሚሊዮን ዶላር፤ ማዕድን 142 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ አሳይተዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግባቸው የግብርና ምርቶች የቅባት እህሎች፣ የጥራጥሬ ምርቶች፣ የብር እና አገዳ እህሎች፣ ጫት፣ እጣንና ሙጫ እና የቁም እንስሳት ሲሆኑ ለእነዚህም ምርቶች የውጭ ንግድ የግብይት ሥርዓት ተዘርግቶላቸው በግብዓት ሥርዓቱ መሠረት ወደ ውጭ እንዲላኩ በማድረግ ለላኪዎች የተለያዩ ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርግ አቶ መስፍን የሚናገሩት።

አቶ መስፍን እንዳብራሩት፤ ከግብርና ዘርፍ የውጭ ንግድ ግብይት የአምስት ወሩ ውስጥ 414 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 272 ነጥብ 8 ሚሊዮን የውጭ ምንዛሬ ገቢ ተገኝቷል። ይህም የቅባት እህሎች፣ የጥራጥሬ ምርቶች፣ የብር እና አገዳ እህሎች፣ የጫት፣ የእጣን፣ የሙጫ እና የቁም እንስሳት ወደ ውጭ በመላክ የተገኘ ሲሆን፤ አፈጻጸሙን በመቶኛ ሲሰላ 65 ነጥብ 8 በመቶ ነው። የውጭ ንግድ ገቢው ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 272 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር ወደ 99 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ አሳይቷል። በባለፈው ዓመት የውጭ ንግድ ገቢ 371 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንደነበር አስታውሰዋል።

የእያንዳንዱ ዘርፍ አፈጻጸም ስንመለከት ከውጭ ንግድ የቅባት እህሎች 69 በመቶ፣ የጥራጥሬ ምርቶች 72 በመቶ፣ ጫት 59 ነጥብ 6፣ የብእርና አገዳ እህሎች 99 በመቶ እና የቁም እንስሳት 50 ነጥብ 3 በመቶ ማከናወን ተችሏል። ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የቅባት እህሎች የውጭ ምንዛሬ ገቢ 40 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ ያሳየ ሲሆን፤ የጥራጥሬ ምርቶች 3ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ አሳይተዋል። የጫትና የቁም እንስሳት የውጭ ንግድ ደግሞ ቅናሽ ማሳየቱ ተመላክቷል።

ለውጭ ንግድ የሚላኩ ምርቶች ቅናሽ ማሳየት እንደምክንያት የሚጠቀሱት በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን የሚናገሩት አቶ መስፍን ፤ የአንዳንድ የጥራጥሬ ምርቶች ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያ መቀዛቀዝ መኖሩን ይገልጻሉ። እንደ አኩሪ አተር እና የማሾ አይነት ምርቶች በዓለም አቀፉ ገበያ መቀዛቀዝ ከታየባቸው ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም በጥራጥሬ እና በጫት ምርቶች እንዲሁም በቁም እንሳሳት የውጭ ንግድ የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋቱን ጠቁመዋል። አንዳንድ ምርቶች ላይ በተለይ ቀይ ቦለቄ፣ ዝንጉርጉር ቦለቄ እና አኩሪ አተር ምርቶች የዓለም አቀፍ ገበያ ዋጋ የመቀነስ ሁኔታዎች በመታየቱ ምክንያት ገቢውን የተሻለ ያለማድረግ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ።

የቅባት እህሎችን ስንመለከት አንዳንድ ምርቶች የኢንዱስትሪ ምርቶች የሚበዙባቸው በመሆኑ የአቅርቦት እጥረት መኖሩን ነው አቶ መስፍን የገለጹት። እንደ ኑግ እና ለውዝ አይነቶቹ ምርቶች በሻጋታ ምክንያት የዓለም አቀፍ አገራት የመግዛት ፍላጎት መቀዛቀዝ የሚስተዋል እንደሆነ ጠቅሰው፤ ዋንኛው የገቢ ምንጭ የሆነው የሰሊጥ ምርት ደግሞ በተበጣጠሰ መልኩ በላኪዎች መያዙ ለውጭ ንግድ ግብይት አቅርቦት እጥረት እንዲከሰት እንዳደረገው አንስተዋል።

አቶ መስፍን እንደሚሉት፤ የጫት ንግድ የድንበር ላይ ጫት ኮታን ሽፋን በማድረግ በኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋቱ በውጭ ንግድ/በኤክስፖርት/ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። በጫት ምርት ላይ አላስፈላጊ ቀረጥ መበራከት ውጭ ንግድ/ ኤክስፖርቱ እንዳይበረታታ እያደረገ ነው። አንዳንድ አካባቢዎች የኬላዎች መበራከት የጫት ምርት በወቅቱ ወደውጭ እንዳይወጣ እንቅፋት እየሆነ መምጣቱ አመላክተው፤ የኮንትሮባንድ ንግድ ለቁም እንሳሳት የዓለም አቀፍ ገበያ መቀዛቀዝ ምክንያት እንደሆነም ያብራራሉ።

የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል ከጉምሩክ ጋር በመቀናጀት የተሰሩ ሥራዎች መኖራቸው የሚናገሩት አቶ መስፍን፤ የድንበር ላይ ኮታዎች እንዲቆሙ በማድረግ ከጉምሩክና ከፌዴራል ፖሊሲ ጋር በመቀናጀት ለመከላከል ጥረት እየተደረገ እንደሆኑ ይናገራሉ። ይህም በመሆኑ በርካታ ለውጦች እየተመዘገቡ ነው ይላሉ። በሌላ በኩል የዓለም አቀፍ ገበያ ዋጋ መቀዛቀዝን ለመከላከል ከኤምባሲዎች ጋር በመሆን የውጭ ንግድ መዳረሻ ከገበያዎች የመለየት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከላኪዎች ጋር ያለውን ችግሮች በመለየት በችግሮቹ ዙሪያ ላይ የጋራ መግባባት በመውሰድ ኤክስፖርቱ እንዲሻሽል ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል። ላኪዎች በገቡት ውል መሠረት ንግዱን እንዲፈጸሙ ለማድረግ የዕለት ተዕለት ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ እንደሆነም አብራርተዋል።

የውጭ ንግድ ላይ የተበራከቱትን ሕገወጦች ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥራ እየተሰራ እንደሆነ የሚገልጹት አቶ መስፍን ፤ ይህንን የበለጠ አጠናክሮ በማስቀጠል የተሻለ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል። በዚህም ለአብነት ለረጅም ጊዜ በጂቡቲና በሱማሌ ሳይሻሻል የቆየው የጫት ንግድ ዋጋ እንዲሻሻል ተደርጓል። ቀደም ሲል 5 ዶላር የነበረውን የጫት ዋጋ አሁን ላይ ወደ 10 ዶላር እንዲገባ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህም በተጨማሪ ከጅቡቲና ከሱማሌ ጋር የነበረው የንግድ ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችል ሰፊ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ጠቁመዋል። በአጠቃላይ የውጭ ንግድ እንዲያሻሽሉ የሚረዱ ሥራዎች በማጠናከር እየተሰራ እንደሆነ ነው አቶ መስፍን የሚገልጹት።

በቀጣይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት በውጭ ንግድ/ኤክስፖርት/ ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ለመፍታት በፖሊሲ መስራት አለበት ያሉት አቶ መስፍን፤ ከክልሎች ጋር በቅንጅት መሥራት ውጭ ንግድ ገበያን በማስፋፋት ኮንትሮባንድ በመከላከል የሚያስችል ሕገወጦች ላይ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ላኪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ የሚሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ የኮትሮባንድ መስመሮች ሰፊ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከጉምሩክ ኮሚሽን እና ከክልሎች በመቀናጀት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ከኤምባሲዎች ጋር በመሆን የገበያ መቀዛቀዙን ለማሻሻል የሚያስችል ሥራ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ ከኤምባሲዎች ጋር በሚሰራ ሥራ ምርቶቹ የሚላኩባቸው አገራት የውጭ ንግድ ግብይት በቀላሉ እና አመቺ በሆነ ሁኔታ ሊካሄድ በሚችልበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑ ያስረዳሉ።

የሩቅ ምስራቅና ኤዥያ አገራት በስፋት የውጭ ንግድ የሚከናወንባቸውና ምርቶች የሚላከባቸው እንደሆነ የሚናገሩት አቶ መስፍን፤ የአውሮፓ አገራት እስካሁን የተወሰኑ ምርቶች ወደ ውጭ ያልተላከባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል። ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ የአውሮፖ አገሮች ጥራት ላይ ትኩረት ስለሚያደርጉ መሆኑን ጠቅሰው፤ አገሪቷ ወደ ውጭ የምትልካቸውን ምርቶች ጥራት ማረጋገጥ የሚችል ላብራቶሪ እንደሚያስፈልጋት ይናገራሉ። ከሌሎች አገሮች ጋር በጥራት ለመወዳደር በጥራት እና መሠረተ ልማት በኩል እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ሲጠናቀቁ የመዳረሻ ገበያዎች እየሰፋ እንደሚመጡ አብራርተዋል።

የንግድና ቀጠናዊ ሚኒስቴር የውጭ ንግድ የአሰራር ሥርዓት ባለማወቅ ሕገወጥ ተግባራት እንደሚፈጸሙ የጠቆሙት አቶ መስፍን፤ በዚህ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በየጊዜው እየተሰሩ በመሆኑ ሚዲያው የሚጠበቅ ድርሻ መወጣት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

> **የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግባቸው የግብርና ምርቶች የቅባት እህሉች፣ የጥራጥሬ ምርቶች፣ የብር እና አገዳ እህሉች፣ ጫት፣ እጣንና ሙጫ እና የቁም እንሰሳት ሲሆኑ ለእነዚህም ምርቶች የውጭ ንግድ የግብይት ሥርዓት ተዘርግቶላቸው በግብዓት ሥርዓቱ መሠረት ወደ ውጭ እንዲላኩ በማድረግ ለላኪዎች የተለያዩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሥራችንን የሚመጥን የሕይወት ታሪክ ለሁላችን

**መስከረም ሰይፉ**

በብዙ የቀብር ስነስርአቶች ላይ ተገኝቼ አውቃለሁ። ብዙዎቹ ሟቾች በሕይወት እያሉ የማላውቀው መልካምና የሚያስቀና አዲስ ማንነት ተችሯቸው የሕይወት ታሪካቸው ሲነበብ ታዝቤያለሁ። እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ ስመለከት ብዙ ጊዜ ለራሴ፤ "ለዚያች ሰዓት ብቻ ፈጣሪ የሟቹን ሕይወት መልሶለት የራሱን የሕይወት ታሪክ የመስማት እድል ቢገጥመው ‹‹እንዲህ ዓይነት ፃድቅ ነበርኩ እንዴ?›› ብሎ ግራ የሚጋባ ይመስለኛል። ያን ሁሉ ያላደረገውን መልካም ሥራና ገድል ሲዘረዘርለት ሲሰማም ‹‹ወይኔ ለካ እንዲህም ማድረግ እችል ነበር?›› በማለት የሚፀፀትም ይመስለኛል።

በቅርቡ አንድ ከልጅነቴ ጀምሮ በማውቀው ሰው የለቅሶ ስነ ስርአት ላይ ያስተዋልኩት ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው። በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ለዚህ ሰው የተነበበለት የሕይወት ታሪክ እንደሌሎቹ ያለቅጥ ተጋንኖ እንኳን ያልሠራውን በችሮታ የሚለግስ የሠራውንም በቅጡ የሚገልጽ አለመሆኑን አስተውያለሁ። ይህ ሰው በአንድ ወቅት የአካባቢው አስተዳዳሪ የነበሩ ሰው፤ እንዲያገለግላቸው ወደ ቤታቸው አምጥተው ቀጥረው ያሰሩት ነበር። እሱ ግን የቀጠሩኝ እርሳቸው ናቸው ሳይል የአካባቢውን ሰው በሙሉ በጉልበቱ ያግዝ ነበር። አብዛኛውን የህይወቱን ጊዜ ሀብታምና ድሀ ሳይል በነጻ የሚያገለግል በሱ ልክ ያገልጋይነትና የቅንነት ልብ ያለው ሌላ ሰው የሚገኝ አይመስለኝም፤ ለዛ ነው በቀብር ስፍራው ጥሩ ሰው ነበር የተባለው አጭር ታሪክ ለሱ ያንሰዋል ያልኩት።

ይህ ሰው ለስራ ወደ ቀዬው ሲመጣ ስንት ዓመቱ እንደነበር ወይም የተወለደበት ዓመተ ምህረት የሚያውቅ ሰው ባለመኖሩ የህይወት ታሪኩ ጅማሬ እኔ ሳገባ እንትናን ያክል ነበር በሚል መላምት ተደመደመ።

ሟቹ አባቴ፣ ወንድሜ አጎቴ...ብሎ የሚያለቅስለት አንድም የስጋ ዘመድ የሌለው ብቸኛ ቢሆንም የቀዬው ሰው ሁሉ ወዳጁ የነበረ ደግሰው ነበረ። ይህ ደግ ሰው አባዬ፣ አባዬ ብሎ የሚያለቅስለት አንድም የስጋ ልጅ ባይኖረውም በደግነቱ የወለዳቸው አያሌ ልጆች ነበሩት። እናም እነዚህ ልጆቹ ከልባቸው አልቅሰውለታል፣ የቀብር ስፍራው አባዬ! አባዬ! በሚል ጩኸት ተደበላልቋል። ባገሬው የለቅሶ ባህል መሰረት ትላልቅ ሰዎች ሲሞቱ እንደሚደረገው በጉራጊኛ "ወርኮተማነረ" እየተባለ በታላቅ የቀብር ሥነሥርዓት ተቀብሯል። "ወርኮ ተማነረ ዋቢ የነበረ ኧኳ ተፈተረ" ትርጉሙም ትልቅ የነበረ ዛሬ አረፈ ደግ የነበር ዛሬ አረፈ እንደማለት ነው።

በዚህም በቀብሩ ዕለት ሴቶቹ እጆቻቸውን እንደ አሞራ ዘርግተው ካገለደሙት ነጠላ ጋር ዘለል፣ ዘለል እያሉ ልብ በሚነካ መንገድ ሙሿቸውን ያወርዳሉ። ወንዶቹም ግርማ ሞገሳም ፈረሳቸው ላይ ሆነው አንዳንዶቹ እራሳቸውን ባለንጋቸው እየገረፉ የወርኮ ተማነር ሥርዓት ክዋኔ ያንቆርቁሩታል። ይህ በጉራጌ ማህበረሰብ የተለመደ የለቅሶ ስነስርአት ነው። ሁኔታው እንኳን የሚያውቁት ሰው ይሁንና ማንንም ቢሆን ያስለቅሳል።

በአገሬው ባህል መሰረት ይህ የለቅሶ ስነስርአት ለተከበሩ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ነበር፣ ታዲያ ይህ ወዳጄ ሀብታም ሆኖ ወይም ጥሩ ቤተሰቦች ኖረውት አይደለም ለዚህ የታደለው፣ መንደሩ ሁሉ የእሱ ውለታ ስላለበት ደግ ሰው ስለ ነበረ ነው፣ በዚህ ጊዜ እንባ እየተናነቀኝ በለቅሶው ቦታ ላይ ቆሜ በትዝታ ወደ ኋላ ነጎድኩ። ይሄ የአካባቢያችን ዋርካ ከላይ ያደፈ ሰማያዊ ካናቴራ መልበስ ያዘወትራል። ወደ አንገቱ ከፍ ብለው ሲመለከቱት መዘዝ፣ መዘዝ ያሉት ኮሌታዎች በርከት ያሉ ካናቴራዎችን ደራርቦ መልበሱን ያሳብቁበታል። ከስር ጥቁር ሱሪ ይለብሳል። ሱሪውን በኮባ ገመድ ወገቡ ላይ ሸብ ካረገ በኋላ ለቅልጥፍና ወይም ለውበት አላውቅም እግሮቹ ጋርም ሱሪውን በዛው በኮባ ገመድ ከባቱ ጋር አዋዶ ይጠፈንጋቸዋል። ሸፈፍ ሸፈፍ ያሉት ተረከዞቹ ጫማውንም ያንሻፍፉበታል። ብዙ የመንደራችን ሰዎች የዋህነቱን እያዩ እንደ ሞኝ እየቆጠሩ ሲስቁበት ብዙ ጊዜ ተመልክቻለሁ።

ይሁን እንጂ ለቅሶ ቦታው ላይ መልካምነቱን ደግነቱን እያነሱ ሲያለቅሱ ህሊናቸው ቢያረፍድም መልካምነት የሚያስቅ ሳይሆን ትልቅ በረከት መሆኑን የተረዱ መስለዋል። ለነገሩ ልጅ ሆኜም ቢሆን ስቀው ሲያበቁ ‹‹እሱ ምን አለበት! የእግዜር ሰው›› ሲሉት ሰምቻለሁ፤ ጥያቄው በእግዜር ሰው ይሳቃል እንዴ? የሚለው ነው። ‹‹እሱ ምን አለበት የእግዜር ሰው!›› የሚሉት የዋህነቱንና ደግነቱን ለመግለጽ ነው።

ሌላው አብሮ ትዝ የሚለኝ ነገር ለልጆች የነበረው ፍቅር ነው፤ ሰውየው ጠላ እጅግ ይወድ ስለነበር ጠላ ባለበት ማህበር ሁሉ ይገኛል። ታዲያ እሱ ጠላውን ብቻ ይጠጣና የሚሰጠውን ዳቦ በኪሱ በሰፈሩ ላለነው ህጻናት ይዞልን ይመጣ ነበር። በእርግጥ ዳቦው በኪሱ ይዞ ስለሚመጣ ኪሱ ውስጥ የነበሩ ብጥቅጣቂ ነገሮች ሁሉ የሙጥኝ ይሉት ነበር፤ ያን ያዩ አዋቂዎች ዳቦውን ስንበላ ፊታቸውን ቢያጨፈግጉም እኛ ግን እጅግ የምንደሰትበት ነገር ነበር። ዛሬ ለቅሶው ላይ ብዙ ወጣቶች አባዬ እያሉ ያለቀሱት እንደዚህ ያለውን ፍቅር ስለቀረባቸው ይሆን ብዬ አስቢያለሁ።

አንዳንዴ ይህን ሰው ሳስብ በአካባቢው ከነበሩ ሰዎች ሁሉ ቀድሞ የሄደ ይመስለኛል። አንዳንዴም ከማህበረሰቡ ለየት ያለ ፍልስፍና የነበራቸውን አደፍርስ እና ጉዱ ካሳን ያስታውሰኛል። በዛች በገጠር መንደር ለሴት ተብለው የተተው ስራዎችን ወደ ጓዳ እየገባ ይሰራ እንደነበር አስታውሳለሁ፤ ይህ በማህበረሰባችን ውስጥ ያልተለመደ ፍልስፍና ነው። ታዲያ በዚ ስራው አንዴ እንኳን ሲመሰገን ሰምቼ አላውቅም፣ ከዛ ይልቅ ወልየ (ሴታሴት) እያሉ ሲሰድቡት ሰምቻለሁ፣ ሰው በህይወት እያለ ማመስገን ነውር የሆነብን ይመስል በቀብሩ ስፍራ ላይ ብዙ ሴቶች ይህንን ደግነቱ እያነሱ ሲያመሰግኑት ነበር።

ለዚያም ይመስለኛል ምንም እንኳን ጠያቂ የስጋ ዘመድ ባይኖረውም አገሬው ተንከባክቦ የጦረው፣ ለቅሶው እንዲያ በአካባቢው ባህል ‹‹ውርኮ ተማነረ›› የቀለጠው። በትዝታ መንጎድ የጀመረው ልቤ በማንነቱ ሲሳብ ሲቀና የታወቀኝ ይሄኔ ነው።

የሰውየው እንዲያ ባመረና በታላቅ ሁኔታ ትንሽ ትልቁ አልቅሶ ቢቀብረውም በማያልቀው መልካም ሥራው ነውና ይገባዋል አልኩኝ። የእንዲህ አይነት ሰዎች የሕይወት ታሪክ ግን ከጸሐፊ ማጣት ብቻ ሳይሆን እንደ አስተማሪም ስለማይቆጠር አላውቅም በበቂ ሁኔታ ሲነገርላቸው አይሰማም። ለሰውየው የሕይወት ታሪክ ጽፎ ከማንበብም በላይ ማሕበረሰቡ በተግባር የሚገባውን ክብር ሁሉ ሰጥቶ በመቅበር ቢክሰውም የእንዲህ አይነት ሰዎች ሥራና ፍልስፍና ግን መነገር አለበት።

ይህን ገጠመኝ ወደዚህ ያመጣሁት እንዲህ አይነት ልብ የማይባሉና የአካባቢን ኋላቀር ልማድ ጥሰው አዲስ አሰራር የሚያሳዩ በጎ ሰዎችም አሉ ለማለት ነው። ብዙ ጊዜ መልካምነት የሚመሰገነው በታዋቂ ሰዎች ሲሆን ነው። ዳሩ ግን የእነዚህን ታዋቂ ሰዎች ምግባር የቀረፀው የእነዚህ ታዋቂ ያልሆኑ ሰዎች አስተወፅዖ ነው። አንድን አካባቢ እንደ ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ የእንዲህ አይነት ግለሰቦች ሚና ከፍተኛ ነው። ማህበረሰብ ደግሞ የእንዲህ አይነት ሰዎች ውጤት ነው። ስለዚህ አዳዲስ አተያይ ያላቸውን ሰዎች ማበረታትና ማስተዋወቅ ይገባናል።

# ዓለም አቀፍ

## በሔናን የቻይና ግዛት ከ80 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በኮቪድ-19 ተያዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሔናን በተባለችዉ በቻይና ግዛት ከ80 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በኮቪድ 19 መያዛቸዉን ቢቢሲ አስነብቧል፡፡

ግዛቷ ጥቅጥቅ ብሎ ከፍተኛ የሕዝብ የሚኖርባት ሦስተኛዋ የቻይና ግዛት ስትሆን ከነዋሪዎቿ 88 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ በኮቪድ ተይዟል ተብሎ ይታመናል። ይህም የጠቅላላ ነዋሪዋ 90 ከመቶ ሕዝብ ማለት ነው።

በጋዜጣዊ መግለጫቸው የግዛቲቱ የጤና ኃላፊ ካን ኹዋንቼንግ እንደተናገሩት፣ 88 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሕዝብ በኮቪድ ተይዘዋል። በቻይና ፍጹም ባልተጠበቀ ፍጥነት ተህዋሲው እንደ ሰደድ እሳት እየተዛመተ ነው። ይህም የሆነው ቻይና 'ዜሮ ኮቪድ ፖሊሲ' የምትለው አቋሟን በቀየረች ቅጽበት ነው።

የሔናን የጤና ኃላፊ ይህ አሐዝ ከመቼ ጀምሮ የተመዘገበ እንደሆነ ባይገልጹም፣ ብዙዎች ግን የእንቅስቃሴ ገደቡ መነሳቱን ተከትሎ እንደሆነ ይጠረጥራሉ።

የሔናን አስደንጋጭ አሐዝ ግን የቻይና ማዕከላዊ መንግሥት እየሰጠ ካለው አሐዝ ጋር ፍጹም የሚጣረስ መሆኑ ተነግሯል።

ማዕከላዊው መንግሥት 1 ነጥብ 4 ቢለዮን ሕዝብ ውስጥ በኮቪድ የተያዘው 120ሺህ ብቻ መሆኑን ሲገልጽ፣ ዜሮ ኮቪድ ፖሊሲ ከተነሳ በኋላ የሞቱት ደግሞ 30 ሰዎች ብቻ መሆናቸዉን ይፋ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት እሑድ ዕለት ለምሳሌ በመላው ቻይና ሦስት ዜጎች ብቻ ናቸው በኮቪድ ምክንያት የሞቱት ብሏል የአገሪቱ መንግሥት።

ቁጥሩ እንዲህ የቀነሰው የቻይና መንግሥት ኮቪድ ተህዋሲ ባስከተለው የጤና መወሳሰብ የሚሞቱ ሰዎች በኮቪድ ሞቱ ተብሎ ሪፖርት እንዳይደረግ መመሪያ ካስተላለፈ በኋላ ነው። የዓለም ጤና ድርጅት ቻይና በኮቪድ የሚሞቱባት ዜጎቿን አሐዝ እየቀነሰች መሆኑ አሳስቦኛል ሲል የገለጸው ባለፈው ሳምንት ነበር።



አንዳንድ የአገሪቱ ግዛቶች ግን ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር የማይስማማ አሐዝ እያወጡ ይገኛሉ። ለምሳሌ የወደብ ከተማ የሆነችው ኪንግዳዎ ከተማ አንድ የጤና ኃላፊ በፈረንጆች ገና ዋዜማ በሰጡት ማብራሪያ በከተማዋ ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ በየቀኑ በኮቪድ ይያዛል ብለው ነበር። ሆኖም ግን ዜናዉ ቶሎ ከድረ ገጽ እንዲነሳ መደረጉንም ተነግሯል።

ይሁን እንጂ ከእሑድ ጀምሮ ቤይጂንግ በተጓዦች ላይ ጥላው የነበረውን እገዳ አንስታለች። ከትናንት ሰኞ ጀምሮ ደግሞ ድንበሮቿን ለጎብኚዎች ክፍት አድርጋለች።

በተቃራኒዉ አንድ የእንግሊዝ የጤና መረጃዎችን የሚያጠናቅር ኩባንያ በቻይና በየቀኑ 14ሺህ ሰዎች በኮቪድ እየሞቱ ነው ብሏል። የቻይና አዲስ ዓመትን ተከትሎ 2 ቢሊዮን ጉዞዎች ይደረጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይህን ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴ ተከትሎ ምናልባት ተህዋሲው ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሊዛመት ይችላል የሚል ስጋትም ተፈጥሯል፡፡

አሜሪካ፣ ካናዳ እና ዩናይትድ ኪንግደምን ጨምሮ በርካታ አገራት ከወዲሁ ከቻይና ለሚመጡ ተጓዦች የኮቪድ ነጻ ሰርተፍኬት እየጠየቁ ነው።



## ሳዑዲ ዓረቢያ የሀጅ ተጓዦች ቁጥርና የእድሜ ገደብ አነሳች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሳኡዲ አረቢያ መንግሥት በሀጅና በዑመራ ተጓዦች ላይ ጥሎ የነበረውን የቁጥርና የእድሜ ገደብ ማንሳቱ ሮይተርስ ዘግቧል።

የሳዑዲ ዓረቢያ የመንግስት ብዙኃን መገናኛ የሀጅ እና ዑምራ ሚንስትርን ጠቅሶ እንደዘገበው መንግስት በአዲሱ የፈረንጆቹ ዓመት በሀጅ ተጓዦች ቁጥር ላይ ገደብ አይጥልም። በተጓዦች እድሜ ላይ ገደቦችም እንደማይኖሩም ተገልጿል።

በፈረንጆቹ 2022 የሀጅ ወቅት የዑምራ መርሐ-ግብሮች በጠንካራ ሁኔታ እንዲቀጥሉ ቢደረግም ኮሮና ወረርሽኝ ውስብስብ ፈተና ደቅኖ ነበር ተብሏል።

በሁለት የሀጅ ወቅቶች ስነ-ስርዓቱ ከሳዑዲ ዓረቢያ ዜጎችና ነዋሪዎች በመጡ ተምሳሌታዊ ቁጥሮች ተገድቦ ቆይቷል።

ሳኡዲ አረቢያ ጥብቅ የጤና ቁጥጥር በማድረግ ባለፈው ዓመት ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ምእመናን ከአገሪቱ ውስጥ ሆነው ስርዓቱን እንዲፈጽሙ ፈቅዳለች።

የተጠናቀቀው የፈረንጆቹ ዓመት የሀጅ የአምልኮ ስነ-ስርዓቱ ያለ ጤና እክል መጠናቀቁን ሮይተርስ ዘግቧል። ምንም እንኳን ከፈረንጆቹ 2021 የሀጅ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 14 በመቶ በላይ የተጓዦች ብልጫ አለዉ፡፡

60 ሺህ አማኞች ብቻ በ2021 በታሪካዊና ሐይማኖታዊው የሀጂ ጉዞ መታደም ችለዋል። ይህ ቁጥር ደግሞ በ2020 ከነበረውና የአማኞች ቁጥር ጋር ሲነጻጸረ ገደቡ ተወሰነ መልኩ ላላ መደረጉ ተገልጿል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ (1923-2013 ዓ.ም)

እፀገነት አክሊሉ

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ አገራችን ካሏት የግዕዝ ቋንቋ ሊቃውንትና ምሁራን ዋነኛው ባለውለታ ናቸው። በግዕዝ ቋንቋችን ዙሪያም የበርካታ መጻሕፍት ደራሲ ናቸው። የግዕዝ ቋንቋን በልጅነት ዕድሜያቸው በተለምዶ የቄስ ትምህርት ቤት ከሚባለው በመጀመር እስከ አሁን ድረስ እየተጠቀሙበትና የእዚህን ብርቅ ቋንቋ ታሪክ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እጅግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉም ናቸው።

ከ1945 እስከ 1951 ዓ.ም አዲስ አበባ በሚገኘው የቅድስት ሥላሴ ትምህርት ቤት ከተማሩ በኋላ በ1952 ዓ.ም ወደ ግብፅ ሄደው በካይሮ ከተማ ኖረዋል። ከዚያም በ1957 ዓ.ም ካይሮ ከሚገኘው የኮፕቲክ ቲዎሎጂካል ኮሌጅ (Coptic Theological College) በቢ .ዲ. (B.D) እንዲሁም ከአሜሪካን ዩኒቨርሲቲ ኢን ካይሮ (American University in Cairo) በቢ.ኤ. (B.A.) ዲግሪ ተመርቀዋል። በመቀጠልም ወደ ጀርመን አገር በመሄድ ከኤበርታርድ ካሪስ ዩኒቨርሲቲ (Eberthard-Karis University) በ1962 ዓ.ም. በሴሚቲክ ፍልስፍና በፒ. ኤች. ዲ. (PHD) ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ለአስር ዓመታት አስተምረዋል።

ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ ከ18 በላይ መጻህፍትን ደርሰዋል። ብዙ መጻሕፍትንና ጽሑፎችንም ተርጉመዋል። እጅግ አድካሚ የሆነውን፣ ነገር ግን የአገር ቅርስን በሥርዓት ለማቆየት የሚያስችለውን የኢትዮጵያን ካታሎግ ማኑስክሪፕት አዘጋጅተው በማይክሮፊልም በማድረግ አዲስ አበባ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ማኑስክሪፕት ቤተ-መጻሕፍት እና ኮሌጅቪል፣ ማይነሶታ ለሚገኘው ለ Hill Monastic Manuscript Library አበርክተዋል።

ከመጀመሪያ ሥራዎቻቸውም በ1965 ዓ.ም. ወደ አማርኛ የተረጐሙት የማርክ ትዌይን (Mark Twain) ኣጫጭር ታሪኮች ኤክስትራክትስ ፍሮም ኣዳምስ ዲያሪ (Extracts from Adam's Diary) የተባለው ነው። ስለ ታዋቂው የጎንዳጎንዳው አባ እስጢፋኖስ በ2006 እና በ2011 ሁለት ጥራዝ መጻሕፍትን ጽፈዋል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው በትርጉም ሥራዎቻቸው የሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎች፣ የአማርኛ፣ ግዕዝ፣ አረብኛ፣ ሂብሩ፣ ላቲን፣ ግሪክ፣ ጀርመንና ኮፕቲክ ናቸው። የግዕዝ ቋንቋን በተመለከተ በርካታ ሥራዎችን በመሥራታቸው ብዙ ሽልማቶችንና ዕውቅናን አግኝተዋል። በበርካታ ዝግጅቶች ላይ በመገኘት ንግግሮችን (lectures) ሰጥተዋል። ግዕዝን አስመልክቶ በብዙ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ቃለ ምልልሶችም ተሳትፈዋል።

በግዕዝ ቋንቋ ላይ ለአበረከቱት አስተዋጽዖ የማካርተር ፌሎውስ ፕሮግራም ጂኒየስ አዋርድ እና የኤድዋርድ ኡሌንዶርፍ ሜዳል ከካውንስል ኦፍ ዘ ብሪቲሽ ኣካደሚ (MacArthur Fellows Program "genius" award and the Edward Ullendorff Medal from the Council of the British Academy) አግኝተዋል።

የዘመናዊና የጥንት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ምሁር የሆኑት ፕሮፌሰር ጌታቸው፣ ያደረጓቸው ምርምሮችና ያሳተሟቸው ጽሁፎች የኢትዮጵያንና የሩቅ ምሥራቅ የክርስቲያን ኃይማኖት አማኝ ወጎችንና ታሪኮችን በማቆየት ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። ጡረታ ከመውጣታቸው በፊት ኮሌጅቪል፣ ሚነሶታ በሚገኘው የሴይንት ጆንስ ዩኒቨርሲቲ Regents Professor of Medieval Studies and Cataloguer of Oriental Manuscripts of the Hill Monastic Manuscript Library በመሆን ሠርተዋል። ከ5 ሺ በላይ ማኑስክሪፕቶችን ካታሎግ በማድረግ የግዕዝን ማኑስክሪፕት በማይክሮፊልም በማስረዳት አስር ካታሎጎችን ኣሳትመዋል። ይህም ምኑም ሳይጓደል በኢትዮጵያ ብቻ የተገኘውን የሄኖክ መጽሐፍን Book of Enoch ይጨምራል። በእውነቱ ይህ እጅግ ከባድ ሥራ ነው።

በባህል ታሪክና ሥነጽሑፍ ችሎታቸውና ተመራማሪነታቸው በአገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ታዋቂነትን ያተረፉ ታላቅ ሰው ነበሩ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ:: ለብዙ ጊዜ በሕመም ቆይተው በ90 ዓመታቸው እንደጎርጎሮሳዊው አቆጣጠር ሰኔ 10 ቀን 2021 ከዚህ ዓለም ዕረፍታቸው ሆነ::

ብዙዎች «የዕውቀት ሁሉ ማህደር» «ተንቀሳቃሽ ቤተመፃሕፍት» ብለው የሚጠሯቸው እኚህ ታላቅ ሰው ዕልፈት ዕውቀት ተጠቅልሎ ወደመቃብር እንደወረደ የሚቆጠር ነው፤ ይላሉ ፕሮፌሰር አዱኛው ወርቁ የኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ተመራማሪ።

«በገና ደርዳሪዎች እንዲህ ትልቅ ሰው ሲሞት
እንግዲህ መቃብር ጠንክረህ ተማር
ፆመ ድጓ ይዞ ገባልህ መምህር ይላሉ::

ብዙ ዕውቀትን ነው ተሸክመው የሄዱት የማይተኩ ሰው ናቸው:: የእሳቸውን ፈለግ መከተል ነው እንጂ እርሳቸው ከሚገባው በላይ ግዴታቸውን ተወጥተው አልፈዋል::»

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ታላላቅ ሰዎች አንዱ ነበሩ:: ቀድሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ያበረከቱት አስተዋፅዎ የጎላ ነው:: ጥንታዊ የኢትዮጵያ መዛግብት ጥናት ላይ እስከዘመናቸው ፍፃሜ ድረስ ገፍተውበት ከፍ ያለ እውቅና አግኝተውበታል::

የታሪክ ምሑሩ ዶክተር አሉላ ዋሴ ከጌታቸው ኃይሌ ጋር



ቤተሰባዊ ቅርርብ አላቸው:: ፕሮፌሰር ጌታቸውን «የባህልና የታሪክ ጠንካራ ዋልታ» «አስተዋይ እና ጥልቅ ዕውቀታቸውንም ለሌሎች ማካፈል የቻሉ ነበሩ» ሲሉ ይገልጿቸዋል::

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በቀድሞው ሸዋ ክፍለአገር በሸንኮራ ወረዳ ከአባታቸው ከግራዝማች ኃይሌ ወልደየስና ከእናታቸው ወይዘሮ አሰገደች ወልደ ዮሐንስ እንደጎርጎሮሳዊው አቆጣጠር ታኅሣስ 19 ቀን 1931 ነበር የተወለዱት። ከቅድስት ሥላሴ ኮሌጅ የመጀመሪያዎቹ ተመራቂዎች አንዱ ሲሆኑ በግብፅ በጀርመን በእስራኤልና በአሜሪካን አገር የከፍተኛ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

ከፍተኛ እውቅና ያስገኘላቸው ጥንታዊ የኢትዮጵያ መዛግብት ጥበቃ ይደረግላቸው ዘንድ ማይክሮ ፊልም በሚባለው ቅጂ መጠበቂያ እንዲመዘገብ ያደረጉት ጥረት፤ በሜኒሶታ ቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርሲቲ በማይክሮ ፊልም ተቀርፀው የሚገኙ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚመለከቱ ጥንታዊ የግዕዝ ሥራዎችን ወደአማርኛ የተረጎሙ። ከእነዚህም መካከል ደቂቀ እስጢፋኖስ፣ የአባ ባህርይ ድርሰቶች፣ ባሕረ ሃሳብ፣ ስለግዕዝ ሥነፅሑፍ የተዘጋጁ አንዳንድ ማስታወሻዎች እና ሌሎች ሥራዎቻቸው ይጠቀሳሉ።

ፕሮፌሰር ጌታቸው በእነዚህ ሥራዎቻቸው በርካታ ሽልማቶችን የተቀበሉ ሲሆን ከአፍሪካ የማርካርተር ሽልማትን ያገኙ ብቸኛው ሰው ነበሩ። ከአሜሪካ መንግሥት በ1987 የተበረከተላቸው የማርካርተር የበሳል አዕምሮና ምጡቅ ተመራማሪ ሽልማት በመስኩ የመጀመሪያው ተሸላሚ አድርጓቸው የ340 ሺህ ዶላር አስገኝቶላቸዋል።

«የማካርተር ፋውንዴሽን ግራንት ያሸነፉት ስለኢትዮጵያ የቆዩ መጽሐፍት ላይ የሚያደርጉት ጥናት እየተረጎሙ በመመዝገብ ከሚያደርጉት ጥናት አንፃር ላደረጉት አስተዋፅኦ የ340 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ነበር ያገኙት። በ1987 ለንደን በሚገኘው የብሪታንያ አካዳሚ አባል እንዲሆኑ ተጋብዘው ሄደው ለአባላት የሚሰጠውን ማዕረግ ፌሎው ኦቭ ዘብሪቲሽ አካዳሚ የሚባለውን አግኝተዋል። አካዳሚው በ83 ዓመት ዕድሜው ውስጥ ከዓለም ሊቃውንት መካከል ዝና ያተረፉትን እየመረጠ ነበረ ለአባልነት ይጋብዝ የነበረው። ከዶክተር ጌታቸው በፊትም ሆነ በኋላ አፍሪካዊ ተጋብዞ አያውቅም። ይኸ ነው አንዱ በውጭ የሚታወቁበት። በ1981 በሱዳን የነበሩና በኋላም አሜሪካ የመጡ ኢትዮጵያውያን ከወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ቡሽና ምክትላቸውን አግኝተው በአቤቱታ መልክ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ አባት ናቸው።»

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ አዘውትረው በየመገናኛ ብዙኃኑ እየቀረቡ ምሑራዊ ሐሳቦችን ሳይሰስቱና ሳይሰለቹ በማቅረብ ዕውቀትን ሲዘሩ ኖረዋል።

ሊቀ ሊቃውንት ጌታቸው ኃይሌንና የሰምና ወርቅ አዘጋጆችን ያገናኘን ከልብ የመነጨ የአገርና የወገን ፍቅር ብቻ ነው። ከዚህም የተነሳ የተቻለንን ያህል በአገራችን ሰዎች መካከል እውቀት የዋዛ ፈዛዛ ቀልድንና ቧልትን ተክቶ እንዲገኝ ለማድረግ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ጥረት አድርገን ብዙ ውጤት አስገኝተናል። ሊቁ እድሜ ልካቸውን ለአገራቸውና ለወገኖቻቸው ያለምንም ክፍያ ወይም ጥቅም አገልግሎት በሰጡበት ጊዜ እርግጥ ነው ሥራቸውን ያጠኑና ጠቀሜታውን ያወቁ ለመልካም ዓላማ የተሰማሩ አንዳንድ ድርጅቶች ለሊቁ ሥራ እውቅናን ለመስጠት የገንዘብ ሽልማት አድርገውላቸዋል። ሆኖም ግን ሊቀ ሊቃውንት ጌታቸው ኃይሌ የተቀበሉትን ገንዘብም ቢሆን አሁንም ለአገራቸው ምሁራን መጠቀሚያ የሚሆኑ የተለያዩ መጻሕፍትን በማሳተም ተጠቀመውበታል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው በጥናቶቻቸው ለረጅም ጊዜና በብዛት የጻፉት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው። በአማርኛ ደጋግሜ ለመጻፍ የበቃሁት በአቶ አምሐ አስፋው እርዳታና ግፊት ነው ይላሉ። የሚደሰቱበት ትልቁ ተግባርም ምዕራባውያን ስለ ኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲያጠኑ የሚጠቀሙት መነጽር ምዕራባዊ እንዳይሆን በጎ ተጽእኖ መፍጠራቸውን ነው። የእርሳቸውን ትሑት አማርኛ ‹‹መፈንቅለ ምዕራብ ወመግረሬ ፀር›› እንለዋለን። ስቴፈን ካፕላን የፕሮፌሰር ጌታቸውን በምዕራባውያን አጥኚዎች መካከል መከሠት (ምጽአተ ጌታቸውን) ‹‹አርዕድ አድለቅልቅ - groundbreaking›› ይሉታል። ምጽአታቸውን መፈንቅል ወይም በቤታችን ቋንቋ መግረሬ ፀር ብንል ሲያንሳባቸው ነው። በትሑት አንደበት ካጫወቱን ማሳያዎችን እንቆነጥራለን።

በአንድ ወቅት መጻህፍቶቻቸው ቀስ በቀስ ወጣቱ እየለመዳቸው እያነበባቸው እንደሆነ ሲሰሙ ‹‹በአማርኛ የምጽፋቸው ተፈላጊነት ማግኘታቸው ደስ ብሎኛል። ግን እኔ ባልጽፋቸውም ሌሎች ይጽፏቸው ነበር።

ለእኔ ትልቅ ደስታ የሰጠኝ በውጪው ዓለም ተመራማሪዎች ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ መፍጠሬ_ነው"። "ሳነብ አገርና ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን የሚጎዳ ነገር ካገኘሁበት በማስረጃ ማስለወጥ እችላለሁ" የምዕራቡን አጥኚ የሚናዝዙ፣ በምዕራቡ ዓለም የነገረ ኢትዮጵያ ጥናት የነፍስ አባት ነበሩ ስንል አንገታችንን ሰገግ ደረታችንን ነፉ አድርገን ነው።

"አንዱ ማስጠንቀቂያዬ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፉ በካቶሊኮች ዐይን እያዩ እንዳይሆን ነው።›› ይላሉ። አውሮፓዊው ሥዕለ ሕሊና ላይ መፈንቅል አድርገዋል ስንል ገቢሩን ዐይተን ሰምተን ነው፡፡

በአውሮፓውያን የኢትዮጵያ ነገረ ክርስቶስ ጥናት ላይ የተካሄደው መፈንቅል እንዲህ ሆነ! ጸጎች በ1870 ዓ.ም. ቦሩ ላይ ተሳደዱ። ግማሹ በግዞት፣ ግማሹ በቅጣት፣ ግማሹ በስደት ተቀጣ። በስደት የሄዱት ወደ ሚሽነሪዎች ተጠግተው አንድ ከባድ በቀል ፈጸሙ። የጸጎች አስተምህሮ ትክክለኛውና ‹‹ተዋሕዶ›› ሊባል የሚገባው የኢትዮጵያ ነገረ ክርስቶስ መሆኑን ጻፉ፤ ተናገሩ። ታመኑ። በእነ ኢግናዚዮ (ኢኛሲዎ) ጉይዲ ተረካቸው ታመነ። ተጻፈበት። የምዕራቡ ዓለም ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለው እይታ እንዲህ ተቀረፀ። ቀረጻው እዚያው አልቀረም። እነ ዶክተር አባ አየለ ተክለ ሃይማኖትም ኢትዮጵያ ላይ አንፀባረቁት። ምስጋና ለእነ መልአከ ብርሃን አድማሱ ይሁንና እዚህ (በሀገር ውስጥ) በስዱዳን ጸጎች የተቃኘው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በጸጋ አስተምህሮ የመመልከት ስሑት እይታ ተቀጨ።

በአውሮፓ ግን እስከ ምጽአተ ጌታቸው ድረስ ይህ ሲሆን አልታየም። ጌች ወደ ምዕራቡ ንፈቀ ክበብ ገቡ። ተገረሙ። መፈንቅሉን ጀመሩት። Material on the Theology of Unctionists, The Faith of Unctionists, Ethiopian Heresies and Theological Controversies, Two Amharic Versions of One Essay in Defense of the Tawahido Faith, ... በመሳሰሉ ሥራዎች የኢትዮጵያን ነገረ ክርስቶስ መሠረታውያን በውስጣዊ እይታ አነጠሩ፤ የምዕራቡን ዓለም በክልኤ ባሕርይ ተወዳጅተው በስሕተት የቀረፁትን ጸጎች "Crypto-Catholic" (መፍቀርያነ ካቶሊክ) ሲሉ ሚስማር መቱባቸው። ምቱ ለጊዜው በእነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌና በመምህራኖቻቸው እነ አለቃ ክፍለ ጊዮርጊስና አለቃ ተክለ ጽን ላይ በማረፉ በአገር ልጅነት ስሜት መሰቀቅ ቢኖርም ዒማላው በሐዲስ ጸጎች ታዝሎ ሊመጣ ያለውን ካቶሊካዊ ተረክ ሳይነሳ ባለበት መምታት ነበረ። ጌች ዒላማውን አልሳቱም! ጉዳዩን በኢንሳይክሎፐዲያ ኢትዮፒካ በሰፈሩ አጫጭር የነገረ ክርስቶስ ጽሑፎችም አትሞታል! በዚህ ምክንያት ያልጐመጐሙ እንደ አባ ተስፋእዝጊ ዑቁቢት ያሉ ትውልደ ኢትዮጵያ/ኤርትራ ካቶሊካውያን አጥኚዎች ቢኖሩም አላገገሙም። የጌታቸውን አሰር የተከተለው የቀሲስ ዶክተር መብራቱ ኪሮስ Mia-physite Christology ተጨምሮባቸዋል። ዋነኛው መግረሬ ፀር ግን እርሱ ነው - ጌታቸው ኃይሌ!

የቆጋው ኢቀኖናዊ ‹‹ሲመት›› በፕሮፌሰር ጌታቸው ዐይን አስቀድመን ፕሮፌሰር ጌታቸው ስለ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽና ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊት ከሚያሰኟት መሠረታውያን አንዱ ብለው በደቂቀ እስጢፋኖስ ተጨማሪ አዲስ መግቢያ ውስጥ ከጻፉልን እንቀንጭብ፡- ‹‹ ሐዋርያዊት ከሚያሰኟት አንዱ መሠረታዊ ምክንያት መሪዋ (ዋናው ጳጳስ) ክርስቶስ ለሐዋርያት የሰጠው ሥልጣን ሲያያዝ መጥቶ ለእሱ ስለደረሰው ነው። ቤተ ክርስቲያናችን ይኸንን ባህል ለመጠበቅ ብዙ ፈተና አልፋለች። መንፈሳው ሥልጣን ስለሚወረስ፥ ጳጳስ ሲሞት በሐዋርየዊት_ቤተ_ክርስቲያን_ሥርዓት_የጵጵስና_ሥልጣን_ባለው_የበላይ_ጳጳስ_እንጂ_የጵጵስና_ሥልጣን_የሌላቸው_ካህናት_ተሰብስበው_ሌላ_ጳጳስ_መሾም_አይችሉም። ስለዚህ ጳጳሳችን በሞተ ቁጥር በብዙ ጥረት ያልተቋረጠ_ሥልጣን ካለው ከግብጹ ፓትርያክ እናስሾም ነበረ። ... የአምላክ ፈቃድ ሆኖ አሁን ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን ችላ የራሷን ፓትርያክ ትሾማለች። ››

እንዳንሳሳት ፕሮፌሰር ጌታቸው የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜን የተማሩት ከሊቀ ጳጳስና ከፓትርያክ ነው። በኢትዮጵያ የሐዲስ ኪዳን መምህራቸው ቀድሞ ሊቀ ሊቃውንት ይባሉ የነበሩትና በጳውሎስ መልእክታት ትርጓሜ የገነኑት ብፁዕ አቡነ_ጴጥሮስ ሲሆኑ በግብፅ ደግሞ የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህራቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ_ሺኖዳ ነበሩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤያትና በሌሎችም ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች እየወከሉ በተደጋጋሚ ቀርበዋል። Ethiopian Liturgical Christology የሚል ጥናትም በጉባኤ አቅርበዋል። ስለ ሃይማኖት ሲጽፉ የተራ ምዕመን ጽሕፈት መስሎን እንዳንሳሳት። ስሕተት ወደሌለበት ዓለም የሄዱትን አባት ነፍስ ይማርልን።

ክብርት ባለቤታቸው ወይዘሮ ምሥራቅ ከፕሮፌሰር ሥራ እና አስተዋጽዖ ተለይተው አይታዩም። ወጣት እያሉ እሳቸው እና ፕሮፌሰር ጌታቸው በጋራ ያሳተሙት "የአዳምና የሔዋን ታሪክ" መጽሐፍ ተጠቃሽ ነው።

ለአገር፣ ለወገን እንዲሁም ለዓለም ጉልህ ድርሻ እያበረከቱ ያሉ ልጆችን ከወይዘሮ ምሥራቅ ጋራ አፍርተዋል። ትልቋ ልጃቸው ዶክተር ርብቃ ጌታቸው በአገራችን እጅግ ዘመናዊ የሆነ አዳሪ ትምህርት ቤት በራሷ ገንዘብ አስገንብታ ትውልድ እያስተማረች ሲሆን፤ ከአራቱ ልጆች ሁለተኛዋ ፕሮፌሰር ሶስና ጌታቸው ደግሞ በአሜሪካ ታዋቂ ሳይንቲስት ናት፤ በቅርቡ በርካታ ሽልማቶችን አግኝታለች። "መልካም ዘር ከነ አገዳው ቸር፤" ይሏል ይሄ ነው።

የፕሮፌሰር ጌታቸውን ዕውቀት፣ አስተዋጽዖ እና ትጋት እንኳን ሊይዙት ጨርሰው ሊዘረዝሩት ይከብዳል። ምናልባት ከሚቀር በአሥር ነጥብ ልግለጻቸው፡-

1. የግዕዝ የብራና መጻሕፍትን ሲያውቋቸው ዘመነኛ ያደርጋቸዋል፤ መጻሕፍቱን ያናግሯቸዋል፤ ትንታኔያቸው ሁሌም ድንቅ እና አዳዲስ ዕውቀት የያዘ ነው። በዓለም አቀፍ ጉባዔያት ላይ ሁሌም ተደማጭና በጉጉት ተጠባቂ ናቸው።
2. የኢትዮጵያ ጥናት ዓለም ዐቀፍ ጉባዔ (Ethiopian Studies) የተሟላ ቅርጽ እንዲይዝ ካደረጉትና በጎ ተጽዕኖ በማሳደር ከምዕራባውያኑ ተጽዕኖ እንዲላቀቅ ካስቻሉ ምሁራን አንዱ ናቸው። በየጊዜው በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ ከመጀመሪያው እስካለፈው ድረስ በመሳተፍና ጥናታዊ ጽሑፍ በማቅረብ ፕሮፌሰር ጌታቸው ወደር የላቸውም። በሌሎች ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ላይ መገኘት ባይችሉ እንኳ ተጠይቀው ጽሑፋቸው እንዲታተም ይደረጋል። እሳቸው የሚያደርጉትን ንግግር ለማዳመጥ አዳራሽ ይሞላል፤ ከእሳቸው ጋር ፎቶ ለመነሳት ፈረንጁ ሁሉ ይጋፋል "እንኳንም የእኛ ሆኑ" ያሰኛል።
3. የግዕዝ ብራና መጻሕፍን አንድ ባንድ ዘርዝሮ በማጥናት፣ እና መዘርዝር (ካታሎግ) በማዘጋጀት ከኢትዮጵያ ብቸኛው ሲሆኑ፣ ለዘርፉ የዓለም አቀፍ ጥናት ሚናቸው ከፍተኛ ነው። ከ5ሺ በላይ የብራና ጽሑፎችን አጥንቶ ካታሎግ በመሥራት በዓለም ውስጥ ብቸኛውና ብዙ መጻሕፍትን ያጠኑ ያደርጋቸዋል።
4. የኢትዮጵያ ታሪክ በተለይ መካከለኛ ዘመን ሲነሳ ተጠያቂ ናቸው። ምዕራባውያን አንዳንዱን ባለማወቅ፣ አንዳንዱን ደግሞ ሆን ብለው ያበላሿቸውን ጉዳዮች በጽሑፋቸው ሞግተዋል፤ አርመዋል። ስለ አገራቸው ኢትዮጵያ ተናግረው አይጠግቡም። የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ሥነ መንግሥት፣ ሥልጣኔ፣ አስተዳደር፣ ፖለቲካ በቅጡ እንዲታወቅ እስከ ሕልፈተ ሕይወታቸው ታግለዋል፤ ጽፈዋል፤ ሞግተዋል።
5. የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተሟላ እንዲሆን ካደረጉት ሊቃውንት መካከል ፕሮፌሰር ጌታቸው ግንባር ቀደም ናቸው። በአጥኚ ክፍተት የነበረውን ጉድለት ሞልተዋል፤ የተረሱ የቤተክርስቲያን ታሪክ አጉልተው አሳይተዋል። ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመን ጀምሮ የቤተ ክህነቱን አስተዳደር በቅርብ የሚያውቁና እንዲስተካከልም በብርቱ ሠርተዋል።
6. የቋንቋ ችሎታቸው እጅግ የሚገርም ነው። ግዕዝ የሙያ/ሥራ/ ቋንቋቸው ሲሆን ጽፈውበታል፣ ተርጉመውበታል፣ አስተምረውበታል። ከሴማውያን ልሳናት ዐረቢ እና ዕብራይስጥ በሚገባ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፤ የማስተካከያ እርማትም ይሰጡባቸዋል። በጽርዕ (ግሪክኛ) (በተለይ ኮይኔ ግሪክ) ይራቀቁበታል። በዚህም የተነሣ የግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ ከሰብዐ ሊቃናት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዴት ወደ እኛ ቋንቋ እንደተመለሰ እና በብርቱ ጥንቃቄ እንደተተረጎመ አሳይተዋል። በዚህም ከእንግሊዝኛ እና አማርኛ ትርጉም ይልቅ የግዕዙ እንደሚበልጥ ያሳያሉ። (ለናሙና "ነቅዐ መጻሕፍት" ገጽ 16-17 ይመለከቷል)። የቅብጢ ቋንቋ (Coptic) እና የላቲን ቋንቋ ጥናትና ምርምር ከሚያደርጉባቸው ቋንቋዎች ውስጥ ናቸው። ከአውሮጳ ቋንቋዎች ጀርመንኛውን ተምረውበት የዱክትርና ምርምራቸውን ጽፈውበታል። የእንግሊዝኛ ቋንቋቸው ፈረንጆችን ያስንቃል።
7. ለአማርኛ ቋንቋ ጥናት በተለይም ለጥንት አማርኛ (Old Amharic) መሬት የሚነቀንቁ በርካታ መጣጥፎች አሳትመዋል። የእርሳቸውን የአማርኛ ጥናት ለሚያነብ ሰው በቋንቋው ዕድገት ከመደነቅም በላይ ቋንቋው በምን ያለ ሳይንሳዊ ዘዴ መጠናት እንዳለት ይማራል። እኔ እንደማስታውሰው ከመጀመሪያዎቹ ምሁራዊ ጽሑፎቻቸው መካከል በJES ያሳተሙት የጥንት አማርኛ ሲሆን፤ የመጨረሻቸው መጽሐፋቸውም ከዚሁ ጋር በተገናኘው ("Teaching and Tradition of the Ethiopian Orthodox Church in Older Amharic") በሚል የወጣ ነው።
8. የሕይወታቸውን ግማሽ ከ 45 ዓመት በላይ የደርግ መንግሥት ባደረገባቸው ግፍ ቆሞ መሄድ ተስኗቸው በወንበር ተወስነው ኖረዋል። ይሄ ግን ጥናታቸውን አልገታውም። "እንዲህ ባለ አስቸጋሪ የጤና ሁኔታ ላይ ሆነው ነው ብዙ የሠሩት፤ አይከብድም?" ሲባሉ ፤ "እግዚአብሔር ብራናዎቹን ቁጭ ብለህ አጥናቸው ሲለኝ ነው የወገብ ታማሚ ያደረገኝ"፤ ብለው የጸና እምነታቸውን ተናግረዋል።
9. እስከ አሁን ያሳተሟቸው እጅግ በርካታ ሲሆኑ ፡- -ከ30 በላይ ታላላቅ መጻሕፍትን በአማርኛ እና እንግሊዝኛ አሳትመዋል። - 8 ቅጽ የግዕዝ ብራና መዘርዝሮች (EMML cat. vol.4-11) ጽፈዋል። - ከ250 በላይ ጥናታዊ ጽሑፎች በልዩ ልዩ ሳይንሳዊ ሕትመቶች ላይ አሳትመዋል። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ከምሁራዊ አስተዋጽኦቸው በተጨማሪ አዲሱ ትውልድ የእርሳቸውን ፈለግ እንዲከተል ጥረት ያደርጉ ነበር።

# ስፖርት





## ኢትዮጵያን በሰርከስ ስፖርት ለማስተዋወቅ የሚተጉ ባለ ራእይ ወጣቶች

ቦጋለ አበበ

የሰርከስ ስፖርት ጅምራቸው በአዲስ አበባ ‹‹አዲስ አፍሪካ ሰርከስ ማህበር›› ውስጥ ነው። ከአስር ዓመታት በላይ አብረው በመስራት ወደ ተለያዩ አገራት በጋራ ጉዞ በማድረግ በስፖርቱ ትርኢቶችን አሳይተዋል። በአብሮነት ቆይታቸው በስፖርቱ ውጤት በማስመዝገብ ወደፊትም ከፍ ብለው አፍሪካን ሊያስጠሩ የሚችሉ ወጣቶች ናቸው። በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ ላስ ቬጋስ 165 ሚሊየን ዶላር በፈሰሰበት ሰርከስ ዱሶሌ ሾው ላይ ተመርጠዉ ስራቸውን ከሚያቀርቡ ወጣቶች መካካል ናቸው። እነዚህ የሰርከስ ስፖርት ጥበበኞች አራት ወጣቶች ሲሆኑ ለገሰ አባ፣ ብሩክ ሞገስ፣ ወንደወሰን ሽመልስ እና ኤፍሬም ፈቃደ ይባላሉ።

ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ ስፖርቱን መስራታቸውን የሚናገረው ብሩክ ሞገስ፣ ወደ ሰርከስ ቡድኑ ከመግባታቸው በፊት ሁሉም በየግላቸው የተለያዩ የሰርከስ ማህበራት ውስጥ ይሰሩ እንደነበር ያስታውሳል። በአንድ ቡድን ውስጥ ተጠቃለው መስራት ከጀመሩ በኋላ አንዳቸው ለአንዳቸው ብርታት በመሆን ራሳቸውን በስፖርቱ በማጎልበት ዛሬ ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። "በዚህ አጋጣሚም የቡድን ሥራ ውጤታማ እንደሚያደርግ አይቻለሁ" ይላል ብሩክ ስለ ሰርከስ ቡድኑ ሲናገር። "እኛ ተግባብተን ተናበን እየሰራን ነው። ስራችንን የምንሰራው ስለዚህ አንዳችን ለአንዳችን ድጋፍ ነን ይህ ደግሞ ገና ከፍ ያደርገናል። ሁሉም በአብሮነት ሥራን ባህል ቢያደርግ ውጤታማ ሆነን የፈለግንበት ቦታ መድረስ እችላለን" የሚል እምነትም አለው።

በዚህ ስፖርት ለዓመታት መዝለቁን የሚናገረው ሌላኛው የቡድኑ አባል ወንደሰን ሽመልስ፣ "የምንሰራው በአገራችን ብዙም ያልተዘመረለት ነገር ግን ቢሰራበት በጣም የሚያዝናና፣ ውጤታማም የሚያደርግ ወጣቶችን ከአጓጉል ቦታዎች ከመዋል የሚታደግ ብዙዎች ራሳቸውን የሚፈትሹበት የስፖርት ዘርፍ የሆነውን የሰርከስ ስፖርት ነው" ይላል።

ለገሰ አባ በበኩሉ፤ ሁሉም ሙያ የራሱ የሆነ ሙያዊ ጥበብ እንዳለው ያስረዳል። ሰርከስ ደግሞ ጥበብን ብቻ ሳይሆን ልዩ ትኩረትን፣ አብሮነትንና መናበብን የሚፈልግ ስለሆነ ብዙዎች አይደፍሩትም። በመሆኑም በአገራችን እንደሌሎቹ ስፖርቶች አይነገርለትም ባይ ነው።



አዲስ አፍሪካ የሰርከስ ማህበር በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ኢትዮጵያን እያስተዋወቀ ይገኛል፣

በተለያዩ አገራት እየዞርን ትርኢቶችን አቅርበናል የሚለው የሰርከስ ቡድኑ አባል ኤፍሬም፤ በጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያንና ዴንማርክ ጥበባቸውን ማሳየት እንደቻሉ ይናገራል። አሁን ደግሞ በአሜሪካ 165 ሚሊየን ዶላር በላይ የወጣበት ትልቅ መድረክ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ለማድረግ ለትርዒቱ ብቁ በመሆናቸው ተመርጠው እየሰሩ መሆኑን ጠቁሟል። ወደፊትም እንደ አህጉር አፍሪካንም እናስጠራለን የሚል እምነት አላቸው።

ይህ የሰርከስ ቡድን አሜሪካ የሚገኝ ትልቅ ተቋም ውስጥ ለመስራትም አጋጣሚውን አግኝቷል። ለዚህ ደግሞ ሰርከስ ዱ ሶሌ ካምፓኒ የራሱን ለሰርከስ ሾው የሚሆኑ አርቲስቶችን ወደ ተለያዩ አገራት በማምራት ውድድሮችን በማካሄድ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎችን ሲመርጥ ቆይቷል። በዚህም ከአፍሪካ ኢትዮጵያ ውስጥ በመገኘት ከተለያዩ የሰርከስ አርቲስቶች ጋር አወዳድረው እነዚህ አራት ወጣቶች መስፈርቱን በማሟላታቸውና የተካሄደውን ውድድር በማሸነፋቸው አሜሪካ ውስጥ ወደሚገኘው ሰርከስ ዱ ሶሌ ካ ተቋም ገብተው በዓለም ላይ ካሉ ትልቁና አስደናቂ በሆነው የሰርከስ መድረክ ላይ ለመስራት ዕድል አግኝተዋል።

ወጣቶቹ የመጀመሪያ የመድረክ ስራቸውንና የተመልካቾችን ግብረመልስ ሲያስታውሱ፣ "በተለያዩ አገራት እንደ አንድ ፕሮፌሽን ስናቀርብ በጣም ደስተኞች ነበርን፤ ምክንያቱም የደከምንበትን ሥራ ለፍሬ ሲበቃ የምናይበት ቀን በመሆኑ። በምናቀርብባቸው ቦታዎች ከተመልካች የምናገኘው አስተያየት አስደናቂ ነዉ፣ ቆመዉም ያጨበጭቡልናል። አክሮባት ሾ ስለሆነም ተወዳጅነት አለዉ አዲስ አበባም ብዙ ሰርተናል" ይላሉ።

እነዚህ ወጣቶች ወደ አሜሪካ በሄዱበት አጋጣሚ ጥበባቸውን ተጠቅመው ኢትዮጵያን በብዙ መንገድ ማስተዋወቅ ችለዋል። በሰርከስ ዱ ሶሌ ተመርጠው የተቋሙ አባል ከሆኑበት ቀን ጀምሮም ይህን ተግባራቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል። በእያንዳንዱ የመድረክ ስራዎቻቸው ላይ ተመልካቾች ኢትዮጵያን እንዲያውቁ ወደ መድረክ በሚወጡበት አጋጣሚ ሁሉ በተለያዩ አርቲስቲክ ስራዎች እያስተዋወቁ ይገኛሉ። ከአፍሪካም ከነዚህ አራት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ውጭ ይህን እድል ያገኘ የለም።

ወጣቶቹ የሰርከስ ጥበበኞች ምንም እንኳን እነዚህን ስኬቶች ቢቀዳጁም ብዙ ፈተናዎችን ማለፋቸውን ያስታውሳሉ። ይህንን ጥበብ ሲጀምሩ ልምምድ የሚሰሩበት ቦታና አልባሳትም አልነበራቸውም፤ የሚዲያ ትኩረትም አያገኙም ነበር። " ይህ ደግሞ በሰዓት መጓዝ የነበረብንን ያህል ርቀት እንዳንጓዝ አድርጎናል። ነገር ግን እኛ ደግሞ ትልቅ ራዕይ ይዘን ስለተነሳን ለነበረብን ችግር እጅ ሳንሰጥ ዛሬ ላለንበት ትልቅ ተቋም ውስጥ ለመግባት በቅተናል" የሚሉት ወጣቶች ከእያንዳንዱ ስኬት ጀርባ የተደላደለ ነገር አይኖርምና መክፈል የነበረባቸውን መስዋዕትነት ከፍለው እዚህ ደርሰዋል።

አላማን ለማሳካት ሲባል ትጋት እንደሚያስፈልግ ለወጣቶች የሚመክሩት የሰርከስ ቡድኑ አባላት፣ "በየትኛውም የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ለምንም ዓይነት ችግር ሳይበገሩ ዓላማቸውን በማስቀደም ወደኋላ ለሚጎትቷቸው ነገሮች ሳይበገሩ ለህልማቸው ቅድሚያ መስጠት አለባቸው" ሲሉም በየትኛውም ሙያ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ካላቸው ጊዜ የተወሰነ ሰዓት ለጥበብ ሙያ ሰጥተው አጓጉል ቦታዎች ላይ ከመዋል ቢቆጠቡ ይመክራሉ። ወጣትነት ብዙ የሚሰራበት፣ የነገ ስንቅ የማዘጋጃ ጊዜ ስለሆነ ለችግር እጅ ሳይሰጡ ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም አለባቸው ይላሉ።

"በተለያዩ አገራት መድረኮችን ስናቀርብ በጣም በርካታ የቴክኖሎጂ እውቀቶችን አግኝተናል፣ ይህንን ቴክኖሎጂ በአገራችን ትልቅና ዓለም አቀፍ የሆነ መድረክ በማዘጋጀት ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም እናስባለን" የሚል ህልም ያላቸው ወጣቶች እነሱ የገጠሟቸውን ችግሮች ሌሎች እንዳይገጥማቸው፣ ወደ ኢትዮጵያ የተለያዩ አርቲስቶች መጥተው ስራዎቻቸውን የሚያቀርቡበት ማዕከል ዘርግተው ትላልቅ መድረኮችን የማዘጋጀት ራእይ ሰንቀው እየተንቀሳቀሱ ነው።


## ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

**የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ከዚህ በታች በተገለጹት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡**

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | ብዛት | የሥራ መደቡ የሚጠይቀው የትምህርት ደረጃና አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | | የሥራ መደቡ የሚጠይቀው ዕውቀት ክህሎት ችሎታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የትምህርት ዓይነት | የትም/ደረጃና አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | |
| 1 | ሴክሬተሪ | IV | በድርጅቱ ስኬል መሠረት | 1 | በሴክሬተሪያል ሳይንስ እና ኦፊስ ማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ | የኮሌጅ ዲፕሎማ እና 2 ዓመት የሥራ ልምድ | የተግባቦት ክህሎት/Communication skill/ያላት |
| 2 | ከፍተኛ ሪፖርተር (ለነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት) | XI | በድርጅቱ ስኬል መሠረት | 1 | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሣይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሣይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | ቢ.ኤ ዲግሪ እና 4 ዓመት ወይም ኤም.ኤ.ዲግሪ 2 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላት | አፋን ኦሮሞ እና አማርኛ ቋንቋዎች የሚችል/የምትችል |

**ማሳሰቢያ፡-**

- አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7/ሰባት/ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ከአንድ ጉርድ ፎቶ ግራፍ ጋር በመያዝ በመ/ቤቱ የሰው ኃብት ስራ አመራር ቢሮ ቁጥር 004 ቀርባችሁ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- የሚያቀርቡት ማስረጃ ከሚያመለክቱት የስራ መደብ ጋር ቀጥታ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት መሆን አለበት፡፡
- የሥራ ልምድ ማስረጃው ላይ የአገልግሎት ዘመን ቀን፣ ወርና ዓ/ም እንዲሁም ይከፈላቸው የነበረውን የወር ደመወዝ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተሰራባቸው የሥራ ልምድ ከሆኑ የሥራ ግብር ስለመክፈሉ መገለጽ እና ከሥራ የተሰናበቱ ከሆነ ከስራ የተሰናበቱበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የሚቀርበው የስራ ልምድ ማስረጃ የመጨረሻው ከተጻፈ 6 ወር ያላለፈው መሆን አለበት፡፡
- የቅጥር ሁኔታ በቋሚነት
- ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ፡፡
- በመ/ቤቱ አሠራር መሠረት ከደመወዝ በተጨማሪ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች ይኖሩታል፡፡
- በዲፕሎማ የት/ት ዝግጅት ለሚወዳደሩ እጩዎች የብቃት ማረጋገጫ (COC) ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ፈተና የሚሰጥበት ጊዜ በውስጥ ማስታወቂያ ሠሌዳ እና በስልክ ይገለፃል፡፡
- እጩ ተወዳዳሪዎች ፈተናውን ካለፉ በኋላ ከሚቀጠሩበት ደመወዝ እኩል ወይም በላይ የሆነ ዋስ/ተያዥ/ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- አድራሻ በላይ ዘለቀ መንገድ ከሰሜን ሆቴል ከፍ ብሎ ወ/ሮ ቀለመወርቅ ት/ቤት አካባቢ፡፡
- ለተጨማሪ ማስረጃ፡- 0111264441 ወይም 0111264469

## የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት